# ወንጌልን የማሰራጫት ዘዴ
# ለወንጌላውያን፥
# ለመጋቢዎች፥ እንዲሁም
# ወንጌልን ለማስፋፋት ለሚያስቡ
# ክርስቲያኖች ሁሉ
# የተዘጋጀ ነው።

በ1994 ዓ.ም (2001 A.D.)
በድጋሚ ታርሞና ተስተካክሎ የተዘጋጀ

አሳታሚ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

የኤስ. አይ. ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል

የመ.ሣ.ቁ.127፥ አዲስ አበባ

# መግቢያ

1. ወንጌላውያንን ማሠልጠን ከክርስቲያን ማኀበረሰብ ዓላማዎች መካከል አንዱ ነው። ይህ ትምህርት አዳዲስ ወንጌላውያንን ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ወንጌላዊ የሚያነቃቃ ትምህርት ያዘለ መጽሐፍ ነው።

2. ለትምህርት ቤትና ለወንጌላውያን ማሠልጠኛ ኮርሶች በተለይ የተዘጋጀ ስለሆነ፥ ወንጌላውያን በግል ደረጃ ቢጠቀሙበት መልካም ነው።

3. በመጽሐፉ ውስጥ ዘጠኝ ትምህርቶች ስለሚገኙበት ለ10 ክፍለ ጊዜ በጣም ጠቃሚ ነው።

4. ወንጌልን ማስፋፋት የጥቂት ሰዎች ብቻ ሳይሆን የጠቅላላ ክርስቲያኖች ተግባር ስለሆነ፥ አንዳንዱን ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ ማስተማር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

# ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ትምህርት 1 | የጌታና የእኛ ሥራ | 1 |
| ትምህርት 2 | የፍቅር ኃይል | 10 |
| ትምህርት 3 | መንፈስ ቅዱስና ቃሉ | 22 |
| ትምህርት 4 | የጸሎት ኃይል | 29 |
| ትምህርት 5 | ስለ ኃጢአት የተሰጠ ትምህርት | 37 |
| ትምህርት 6 | የደኅንነት መልእክቶች | 48 |
| ትምህርት 7 | ሰዎች ክርስቶስን እንዲቀበሉ መርዳት | 54 |
| ትምህርት 8 | መመስከርና መምከር | 61 |
| ትምህርት 9 | የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት | 65 |
| የጥያቄዎች | መልስ | 68 |

# ወንጌልን ማስፋፋት

# ትምህርት 1

# የጌታና የእኛ ሥራ

ወንጌልን ማስፋፋት

ወንጌልን በማስፋፋት ላይ የእግዚአብሔር ሥራ

ወንጌልን በማስፋፋት ላይ የእኛ ተሳትፎ

## 1. ወንጌልን ማስፋፋት ማለት ምን ማለት ነው?

ወንጌልን ማስፋፋት የሚለውን ርእስ ስትሰሙ ምን ይሰማችኋል? . . . የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች? ስብሰባዎች? ወንጌልን ማስፋፋት?

ወንጌልን ማስፋፋት የወንጌልን የምሥራች ለሕዝብ ማሰማት ማለት ነው።

ሆኖም የምሥራቹን መናገር ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ እንዲሠራበትና ክርስቶስንም እንደ አዳኙ እንዲቀበለው እንፈልጋለን።

ሀ. ወንጌልን የማስፋፋት ትርጉም

ዓላማ፡- በዚህ ትምህርት ውስጥ ወንጌልን ስለ ማስፋፋት ለማስረዳት ነው።

በግሪክ ቋንቋ ወንጌል «የምሥራች» ማለት ነው።

ወንጌልን ማስፋፋት፡- ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተባብረን ሕዝቡ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኙ እንዲያምንና እንደ ጌታም እንዲያገለግለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማቅረብ ነው . . . ለዚህ ወንጌልን ማስፋፋት ስለሚለው ትምህርት የምንሰጠው ትርጉም ይህ ነው።

የሚወሰደው እርምጃ፡- ክርስቶስን ማቅረብ

ኃይል፡- የመንፈስ ቅዱስ

ዓላማ፡- ሕዝቡ ክርስቶስን እንደ አዳኙ አድርጎ እንዲያምንበት

ውጤቶች፡- ከቤተ ክርስቲያን ጋር በመቀላቀል ክርስቶስን እንደ ጌታ አድርጎ ማገልገል።

ለ. ወንጌልን ለማስፋፋት የተሰጠን መብት

ዓላማ፡- ወንጌልን ለማስፋፋት ስለተሰጠን መብት ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ ለማንኛውም ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንደምንችል ለማሳየት ነው።

በሌላ ሃይማኖት ወደሚያምነው ሰው ሄደን ወንጌልን ለመመስከር ምን መብት አለን? በአብዛኛዎቹ ሃይማኖቶች ውስጥ መልካም ትምህርቶች አሉ። ስለዚህ ሰዎች እምነታቸውንና ልማዳቸውን እንዲለውጡ ለማድረግ የምንመሰክረው ለምንድን ነው? ወንጌልን የምንሰብከው በማን ሥልጣን ነው? ማቴ. 28፡18–20 አንብቡ። እነዚህን ጥቅሶች በቃላችሁ አጥኑ። ዓለምንና በውስጡ ያለውንም ሁሉ የፈጠረው አንዱ እና እውነተኛው የፍጥረተ ዓለሙ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ቃሉን በዚህ ምድር ለሰው ሁሉ እንድንናገር አዝዞናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ይህን ትእዛዝ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷል። ይህንንም «ታላቁ ተልዕኮ» ብለን ሰይመነዋል። የእግዚአብሔር ቃል ወንጌልን እንድናስፋፋ በማዘዝ መብት ሰጥቶናል።

| የፈቃድ ምስክር ወረቀት | |
|---|---|
| ለሚመለከተው ሁሉ፡- | |
| በእኔ የሚያምን ሁሉ ስለ እኔ እንዲመሰክርና የማዳኔን የምሥራች በቃሌ ትእዛዝ መሠረት ለሰው ሁሉ እንዲነግር ፈቅጄለታለሁ። | |
| የሐዋ. ሥራ 1፡8<br>ማቴ. 28፡18–20<br>ማር. 16፡15–16 | በሰማይና በምድር ሙሉ ሥልጣን ያለው።<br>ኢየሱስ ክርስቶስ |

ኢየሱስ «ሂዱ» ያለው ወዴት ነበር? (ወደ አሕዛብ ሁሉ፥ ወደ ዓለም ሁሉ።) እንድንሄድ ያዘዘን ማን ነው? (የዓለም ሁሉ አምላክ።)

ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን በምትሰብክበትና ስለ ኢየሱስም በምትናገርበት ጊዜ መከራ ደረሰባት፤ ስለ ኢየሱስም እንዳትናገር ተከለከለች። እርሷ ግን የእግዚአብሔር ሥልጣን ከሰዎች ሥልጣን የሚበልጥ መሆኑን ተረድታ መስበኳን ቀጠለች (የሐዋ. 5፡29)።

## ሐ. ወንጌልን ለመስበክ ያለው መሠረታዊ የሥራ ዓይነት

ዓላማ፡- ሦስቱን ዓይነት የወንጌል ማስፋፋት ሥራዎች ለማስተማር ነው። እናንተም በምትኖሩባቸው አካባቢዎች በእያንዳንዱ ዓይነት እንዴት ልትጠቀሙባቸው እንደምትችሉ ተወያዩበት።

ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ ኢየሱስ ክርስቶስን በቀላሉ የምናቀርብበት መንገድ ነው። ሰዎችም እርሱን እንደ አዳኛቸው እንዲቀበሉትና እንደ ጌታቸውም እንዲያገለግሉት የምናስተምርበት ዕቅድ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት ዘዴዎችን እንመለከታለን። አንዱም ሌላውን እንዴት አድርጎ እንደሚያጠናክረው እናያለን።

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴያቸውን ከጊዜው ሁናቴ ጋር እንዲስማማ አድርገዋል። ለወንጌል ማስፋፊያ ሥራቸው መሠረት የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር። መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥ በመኖር በእነርሱም አማካይነት ይሠራ ነበር። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነታቸውን ሲጠብቅላቸው በየአጋጣሚውም ሁሉ መልእክቱን እንዲሰብኩ እግዚአብሔር ብርታትን ሰጥቷቸዋል።

እግዚአብሔር በመሠረታዊው ዘዴ አሠራር እንዲጠቀምብን መፍቀድ አለብን። ስለ ዘዴዎቹ ስንናገር የወንጌልን መልእክት እንዴት ለማቅረብ እንደምንችል መግለጻችን ነው። ጌታ ለተከታዮቹ የነገራቸው ሦስት ዓይነት መሠረታዊ ዘዴዎች አሉ።

1. መስበክ፡- ወንጌልን ማወጅ (በአደባባይ ማስታወቅ) ሰዎች ኃጢአታቸውን ትተው አዳኛቸውን እንዲቀበሉ መስበክ (ማር. 16፡15)።

2. ማስተማር፡- በወንጌል ውስጥ የሚገኙትን እውነቶች ማስረዳት፥ ሰዎች የተማሩትን ትምህርት በኑሮአቸው ውስጥ እንዲጠቀሙበት መርዳት (ማቴ. 28፡19)።

3. መመስከር፡- ክርስቶስ ለእኛ ምን እንዳደረገልን ለሕዝብ መናገር (የሐዋ. ሥራ 1፡8)።

## 2. ወንጌልን በማስፋፋት ላይ የእግዚአብሔር ሥራ

### ሀ. ወንጌልን በማስፋፋት ላይ የእግዚአብሔር ዕቅድ

ዓላማ፡- ወንጌልን ለማስፋፋት ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ዘርዝሮ ለማስረዳት ነው።

የወንጌል ትምህርት እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ሰዎችን ለማዳን ያቀደው ታላቅ ዕቅድ አካል ነው። እግዚአብሔር ኃጢአት ሰውን ከእርሱ! እንደሚለይ ያውቃል። ይህም ኃጢአት የግድ በሞት መቀጣት ነበረበት። ስለዚህም ኃጢአት በሞት እንዲቀጣ ያስፈልግ ነበር። አንድ ኃጢአተኛ ለመዳን ያለው ብቸኛ መንገድ አንድ ንጹሕ የሆነ ሰው የእርሱን ቦታ እንዲወስድ ማድረግ ነበር።

እግዚአብሔር ራሱ የሰውን ኃጢአት ለመውሰድ ዕቅድ ነበረው። እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ በእኛ ምትክ ሞተ፥ እንደገናም ተነሣ እርሱም እንደ አዳኛቸውና እንደ ጌታቸው አድርገው ለሚቀበሉት ሁሉ የዘላለም ሕይወትን ይሰጣል። መንፈስ ቅዱስ በሚያምኑት ሁሉ ውስጥ ለመኖር ይመጣል። አዲስም ባሕርይ ይሰጣቸዋል። የኃጢአትን ኃይል ሰብሮ የእግዚአብሔር ልጆች ያደርጋቸዋል።

እግዚአብሔር መልካሙን የቤዛነት ዜና በዓለም ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ የሚያደርሱ መእልክተኞች ያስፈልጉታል፤ የዳኑት ሁሉ መልእክተኞቹ ናቸው፤ እነዚህም ምስክሮች ይሆኑለታል፤ ስለማዳኑ ሥራ የሚናገሩት ቃል እውነት መሆኑን ሕይወታቸው ያረጋግጣል።

አዳኙ ከእነርሱ ጋር ይሄዳል፤ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ አማካይነት ይሠራል፤ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ያንጻሉ፤ እርሷም ከክርስቶስ ጋር በሥራውና በቤዛነቱ የተቆራኘች ናት። የእግዚአብሔር ወንጌልን የማስፋፋት ዕቅድ በአብያተ ክርስቲያናት አማካይነት በመሥራት ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ማዳረስ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ወንጌልን ለማስፋፋት ያከናወናቸው ተግባራት

ዓላማ:- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወንጌል መስበክን የሚመስሉ የሥራ ዓይነቶችን ለመጠቆም ነው።

1. እግዚአብሔር በዔድን ገነት

   ሀ. በዔድን ገነት ውስጥ እግዚአብሔር አዳምን ፈለገው (ዘፍ. 3፡8)።

   ለ. እግዚአብሔር ለጠፉት ሰዎች ያለው ፍቅር እነርሱ የትም ሀታ ቢደበቁም እንኳ እርሱ ካሉበት ቦታ ያደርሰዋል።

   ሐ. እግዚአብሔር እነርሱን በመውቀስ ፈንታ ፍቅሩን ገለጸላቸው፤ ከእርሱም ጋር ያላቸውን ወዳጅነት መልሶ ለማደስ ስለ እነርሱ መሥዋዕት አቀረበ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ ሲጠራቸው እንመለከታለን፤ በመልእክተኞቹም በኖኅ፥ በዮናስ፥ በኢሳይያስ፥ በኤርምያስ፥ በአሞጽና በሌሎችም አማካይነት እንዲድኑ ይጠራቸው ነበር፤ ዛሬም የእግዚአብሔር ማዳኛ ዘዴው ይኸው ነው።

የእግዚአብሔር መልእክተኞች ስለሆንን የጠፉትን መፈለግ አለብን፤ በስማቸው ልንጠራቸውና ልንጠይቃቸው ይገባናል፤ እንዲሁም ጥፋታቸውን ልንገልጽላቸው ያስፈልጋል፤ የኃጢአትንም

ውጤት ልናሳያቸው ይገባል፤ ይልቁንም ከሰይጣን ኃይል ነፃ ስለሚያወጣቸው አዳኝ ማስረዳት ይኖርብናል። የደኅንነት መሥዋዕት በጎልጎታ ተሠውቶአል፤ አማኞችም እንደዚሁ ሌሎቹን ለመርዳትና ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ ለማድረግ ለራስ ወዳድነት መሞት አለባቸው። ሕያው መሥዋዕት መሆን አለብን (ሮሜ 12፡1–2)። ስለ እግዚአብሔር ፍርድ አሰጣጥ ስንገልጽ ስለ ፍቅሩም ጭምር መናገር ይኖርብናል፤ ኃጢአተኞችና ሕዝቡም በእኛ ያለውን የእርሱን ፍቅር ሊያዩ ይገባል። የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ማለት የእግዚአብሔር በሰዎች ውስጥ አድሮ መሥራት ማለት ነው።

2. እግዚአብሔር በሐዋርያት ሥራ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በተራ ሰዎች ተጠቅሟል፤ ለተከታዮቹም በእነርሱ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ እንደሚሠራ ተስፋ ሰጥቶቸዋል፤ ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው የገንዘብ ወይም የአካል ዋስትና ለማግኘት አልፈለጉም። ነገር ግን በየቀኑ በአደጋ ውስጥ ይገኙ ነበር፤ ወኅኒ ቤት ይታሰሩና ይደበደቡም ነበር፤ ለሚሰብኩላቸው ሰዎች ቀንና ሌሊት በእንባ ይጸልዩላቸው ነበር። የእምነት ሰዎች ነበሩ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ያምኑ ነበር፤ በኢየሱስ ስም በሚሰብኩበት ጊዜ ውጤት ለማግኘት ይጠባበቁ ነበር፤ እግዚአብሔር የሰጠውንም ተስፋ አምነው ተቀብለዋል፤ እርሱም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእነርሱ ጋር እንደሚኖር ተስፋ ሰጥቷቸዋል፤ ስለዚህ በእርሱ ስም ሽባውን ተነሥቶ በእግሩ እንዲቆም አዘዙ፤ ስደትን መቋቋም የቻሉት በዚህ ምክንያት ነው፤ እየዘመሩና እየጸለዩ ከእሥር ቤት ወጡ። ጳውሎስ በድንጋይ ከተወገረና የሞተ ሰው መስሎ ከወደቀ በኋላ እንደገና ተነሥቶ ወንጌልን ሰበከ። እምነታቸው የተመሠረተው ሕያው ሆኖ ከሙታን በተነሣው በክርስቶስ ላይ ነበር።

ሐ. ወንጌልን ለማስፋፋት የሚሰጠው የእግዚአብሔር ኃይል

ዓላማ፡– የእግዚአብሔርን ኃይል ለማወቅና በእኛም እንዲጠቀምብን ለመሻት እንዲያስችለን ነው።

የወንጌል ማስፋፊያ ዘዴ፤ የምንናገራቸው ቃላት፥ የምንሠራው ሥራ ወይም የአኗኗራችን መሠረት የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ያለ እግዚአብሔር ኃይል የእኛ ጥረት ሁሉ ከንቱ ነው። ለዓለም ልናቀርብላት የሚገባን ሕያው የሆነውን ክርስቶስን ነው። የኃጢአትን ሰንሰለት የሚበጥስና የእግዚአብሔር ልጆች ለማድረግ ሰውን ነፃ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው።


እውነተኛው የወንጌል መስፋፋት ሥራ መካሄድ ያለበት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

## 3. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ የእኛ ተሳትፎ

### ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ተሳትፎ

ዓላማ፡- ከእግዚአብሔር ጋር ማኅበርተኞች መሆናችንን ማመንና ከዚሁም የተነሣ የምናገኘውን ኃላፊነት ተገንዝበን እንድንቀበል ለማስረዳት ነው።

እግዚአብሔር የወንጌልን ማስፋፋት ሥራ የሚያካሂደው በሕዝቡ አማካይነት ከሆነ የእኛ ኃላፊነት እርሱ እንደ ፈቃዱ እንዲሠራ ለእርሱ መተው ነው፤ እግዚአብሔር ዕቅዱን በጠቅላላው ይቆጣጠራል፤ የተለያዩ ሰዎችንም ለተለያዩ ኃላፊነቶች ይመርጣቸዋል፤ እግዚአብሔር ትእዛዛትን ይሰጣል፤ ይኸውም አንዱን ክፍል ለቤተ ክርስቲያን ሌላውን ክፍል ደግሞ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ያድላል (1ኛ ቆሮ. 3፡9–10)።




ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ተመልከታችሁ እግዚአብሔር በእያንዳንዳቸው ላይ የራሳችሁን ኃላፊነት እንዲያሳያችሁ ጠይቁት።

1. ዮሐ. 15፡4–5 እና ማቴ. 5፡13–16
2. ማቴ. 9፡35–38፤ ሉቃ. 10፡1–2 እና ዮሐ. 4፡35
3. የሐዋ. ሥራ 1፡8 እና ሉቃ. 24፡47–49

4. ማር. 16፡15—18፤ ማቴ. 28፡19—20 እና ዮሐ. 20፡21—22 እያንዳንዱን የጥቅስ ክፍል አንብባችሁ የራሳችሁን ኃላፊነት ጥቀሱ።

ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ተሳትፎ ማለት ጊዜያችንን፥ ችሎታችንን፥ ገንዘባችንን፥ ቤታችንን፥ ንብረታችንንና ልጆቻችንንም እንኳ ቢሆን እርሱ እንደ ወደደ እንዲጠቀምባቸው መስጠት ማለት ነው። እግዚአብሔር እኛ በእርሱ እንድንሞላና በእኛ አማካኝነት ሊሠራ ይፈልጋል፤ የእርሱ ድምፅ፥ እጆችና እግሮች ሆነን ወደ ጠፉት ሰዎች እርሱን እንወስደዋለን።

ለእያንዳንዱ አጋጣሚ መልእክቱን እንቀበላለን። ከእርሱ ጋር በጸሎት በምንገናኝበትና ቃሉን በምናጠናበት ጊዜ ለማንኛውም ዓይነት ችግር እርዳታ እናገኛለን።

ለ. ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለን ተሳትፎ

ዓላማ፡— እኛ ወንጌልን በማስፋፋት ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ዘርዝሮ ለማስረዳት ነው።

ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ ማኅበራዊና ግላዊ ኃላፊነት ነው፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡12—27 አንብቡ። እያንዳንዱ የክርስቶስ አካል በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ተካፋይ የሚሆንበት የራሱ የሆነ ድርሻ አለው፤ ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያዛል።

ሐ. ከጠፉት ሰዎች ጋር ያለን ተሳትፎ

ዓላማ፡— ለጠፉት ሰዎች ባለን ከባድ ኃላፊነት ስለ እነርሱ ለማሰብና እነርሱንም ወደ ክርስቶስ መልሶ ለማምጣት ፍላጎት እንዲኖረን ለማድረግ ነው።

- በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ያለን ተሳትፎ እግዚአብሔርን ለማያውቁ ሰዎች የምናቀርበው አገልግሎት ነው።
- በመንፈሳዊ ረሃብ ለሚጨነቁ ሰዎች የሕይወት እንጀራ እንድናቀርብላቸውና በኃጢአትም እስራት ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች የምሕረትን አዋጅ እንድናሰማቸው ነው።
- ለእነዚያ ለጠፉት ሰዎች እርሱ ክርስቶስ መንገድና እውነት ሕይወትም እንደሆነ የሚያሳይ ወደ እግዚአብሔር መንገድ የሚወስድ ካርታ መጽሐፍ ቅዱስ አለን።

- በዓለም ውስጥ የሚፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ ስንመለከታቸው ጌታ ከመመለሱ በፊት በመጨረሻው ዘመን ውስጥ የምንገኝ መሆናችንን ያሳስቡናል፤ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን ሁሉ በዚህ በታላቁ የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ላይ ተካፋዮች እንዲሆኑ ይጠራል።

መ. ከሰይጣን ጋር ያለን ጦርነት

ዓላማ፡- የወንጌልን ማስፋፋት ሥራ ለማሰናከል በመሞከር ሰይጣን የሚጠቀምባቸውን አንዳንድ መንገዶች ለመጥቀስ ነው።

ወንጌልን ስንሰብክ የሰይጣንን እሥረኞች ወይም ባሮች ነፃ ለማውጣት መሞከራችን ነው፤ ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት አይችሉም፤ እኛም ብንሆን ነፃ ልናወጣቸው አንችልም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ነፃ ሊያወጣቸው እንደሚችል እንነግራቸዋለን። ስለዚህም ከሰይጣን ጋር ቀጥታ ጦርነት ማድረጋችን ነው፤ ሰይጣን በዔድን ገነት ውስጥ ሔዋንን ካሳታት ጊዜ ጀምሮ ከሰው ጋር ጦርነት እንዳደረገ ነው፤ ሰይጣን እናንተን ይዋጋችኋል፤ በሚቻለው መንገድ ሁሉ የወንጌልን ማስፋፋት ሥራ ለማሰናከል ይሞክራል። ሰዎች እውነትን እንዳያዩ ያሳውራቸዋል፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡4 አንብቡ።

ሰይጣን ደንዳኖች ማድረግ ብቻ ሳይሆን ምንም ዓይነት ነገር እንዳይሰማን ያደርጋል። ይህንንም የሚያደርገው ተስፋ እንድንቆርጥና ለምንም የማንረባ ነን ብለን እንድናስብ ነው። ስደት፥ ጥርጥር፥ ነቀፋ፥ ሽብር፥ አለመግባባት፥ ስሜታዊ ግፊት፥ እንዲሁም አካላዊ ሕመም እንዲደርስብን ያደርጋል።

ከሰይጣን ጋር ያሉን እነዚህ ውጊያዎች ሁሉ ከወንጌል ማስፋፋት ሥራችን ጋር የተያያዙ ናቸው። ከሰይጣን አሠራር ዘዴ ልንጠነቀቅና እግዚአብሔርም ያዘጋጀልንን መከላከያ ጋሻ ልንጠቀምበት ይገባል።

1. ጦርነቱ ከሰይጣን ጋር እንጂ እኛን ከሚቃወሙ ሰዎች ጋር አለመሆኑን ልንረዳ ይገባናል፤ ይህንንም ስናደርግ የምናነጋግራቸው ሰዎች ደንዳኖችና የማይሰሙን ቢሆኑም እንኳ በትእግሥትና በማስተዋል ከእነርሱ ጋር መሥራት ይገባናል።

2. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ሳቢያ የሚመጣውን አደጋ ልንፈራ አይገባም፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሄዳል፤ መንፈስ ቅዱስና ብርሃን የሆነው የእግዚአብሔር ቃል በልባችን ውስጥ እየሠራ መንፈሳዊ አስተዋይነትን ይሰጠናል።

ኤፌሶን 6፥10–18 አንብቡ። የክርስቶስ ወታደር እንደመሆናችሁ መጠን የእግዚአብሔር የጦር ዕቃዎች ሁሉ አሉአችሁ። ሰይጣንን ኢየሱስ በመስቀሉ ድል አድርጎታል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሰይጣን ላይ ድልን ልናውጅበት እንችላለን፤ 2ኛ ቆሮ. 6፥1 አንብቡ።

## ጥያቄዎች

1. የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ትርጉም ምንድን ነው?

2. አንድ አማኝ ወንጌልን እንዲሰብክ የፈቀደበትን ጥቅስ ገልጸህ አስረዳ።

3. ሦስቱን ዓይነት የወንጌል ማስፋፋት ሥራዎች በዝርዝር ግለጽ።

4. እግዚአብሔር ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ ያቀደው ለምንድን ነው?

5. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ የእግዚአብሔር መልእክተኞች እነማን ናቸው?

6. ስለ ወንጌል ማስፋፋት ሥራ እግዚአብሔር ያለውን ዕቅድ የሚገልጽ ንድፍ ሥራ።

7. እግዚአብሔር ለአዳም ሊገልጽለት የፈለገው የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ምንድን ነው?

8. ሰዎችን ለማዳን ክርስቶስ በመሥዋዕትነት ተሠውቷል፤ አማኙስ ማቅረብ የሚገባው ምን ዓይነት መሥዋዕትነት ነው?

9. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ላይ እኛ ያለንን ተሳትፎ የሚያሳዩትን መንገዶች በዝርዝር አስረዳ።

10. ወንጌልን ስለ ማስፋፋት ለሰዎች ሁሉ የተሰጡት ኃላፊነቶች አንድ ዓይነት ናቸው?

11. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ያላት ተሳትፎ ምንድን ነው?

12. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ጠቃሚዎች ሆነን እንድንሠራ እግዚአብሔር እኛን እንዲቆጣጠረን የምንፈቅድለት ነገር ምንድን ነው?

13. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ላይ ተቃዋሚ የሆነው ጠላት ማን ነው? ለማሰናከልም የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?

14. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ላይ ከሰይጣን ጋር በምናደርገው ጦርነት ልናውቃቸው የሚገቡንን ሁለት ነገሮች በመጥቀስ አስረዳ።

(መልሶቹ በመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተሰጥተዋል።)

# ትምህርት 2

በትምህርት ሁለት ውስጥ የፍቅርን ዘጠኝ ገጽታዎች እንመለከታለን። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

## የፍቅር ኃይል

1. ፍቅር በባሕርያችን ላይ

   ሀ. የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ላይ

   ለ. በሰዎች ላይ ያለን ሁኔታ

   ሐ. ለራሳችን ያለን አመለካከት

2. የፍቅር ግፊት

   ሀ. የእግዚአብሔር ትእዛዝ

   ለ. ከሕዝቡ ጋር

   ሐ. ከራሳችን ጋር

3. ለፍቅር የምንገባው ግዴታ

## 1. ፍቅር በባሕርያችን ላይ

ማንም ሰው በሕይወቱ ውስጥ መጽናቱን ወይም መውደቁን የሚገምተው በራሱ አቋም ነው፤ ይህም በተለይ ወንጌል በማስፋፋት ሥራ ላይ እውነት ሆኖ ይገኛል። የእኛ ሁኔታ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ሊስብ ወይም ከእግዚአብሔር ሊያርቅ ይችላል፤ ፍቅር ይስባል። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ሕዝቡን ወደ እርሱ ሊስብ ይችላል። ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ ልባዊ የሆነ ትምህርትና ስብከት ወይም ምስክርነት የሚበልጥ ነው። የእኛ ሁናቴ ፍቅርን ይገልጻል ወይም የፍቅርን መጉደል ያመለክታል፤ ይኸውም ለእውነተኛው የወንጌል ማስፋፋት ሥራ በጣም ተፈላጊ ነው፤ ይህም ማለት እግዚአብሔርንና ሰውን ማፍቀር ማለት ነው። እግዚአብሔርን መውደድ ማለት እርሱ በእኛ እንዲጠቀምብን ራሳችንን መስጠት ማለት ነው፤ ሰውን መውደድ ማለት ሕዝብን ወደ እግዚአብሔር ለመሳብ የሚችል የአገልግሎት ቁልፍ ማለት ነው። የእግዚአብሔር

ፍቅር በሕይወታችን ውስጥ የሚገዛ ኃይል ነው። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰዎች እንዲሁም ስለ ራሳችንም ትክክለኛ የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ያስችለናል።

ሀ. የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ላይ የሚያስከትለው ውጤት

(2ኛ ቆሮ. 5፥14-15)

ዓላማ፡- በእግዚአብሔር ላይ ያለን ፍቅር በወንጌል ሥራ ላይ እንዴት እንደሚያተኩር ለማስረዳት ነው።

እግዚአብሔርን የምናገለግለው እርሱን በመፍራት ወይም በፈቃደኝነት ላይ ባልተመሠረተ ሁኔታ ከሆነ የወንጌልን እውነት በተሳሳተ መንገድ ተርጉመነዋል ማለት ነው። ወንጌል ማለት እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ፍቅር የምሥራች መንገር ማለት ነው (ዮሐ. 3፥16)።

የቱን ያህል እግዚአብሔር እኛን እንደሚወድ እየተረዳን በሄድን መጠን የበለጠ እርሱን እንወደዋለን፤ የእኛም ሁኔታ ከፍርሃት ወደ ማመን፥ ከመሸፈት እርሱን በፈቃደኝነት ወደ ማገልገል ይለወጣል፤ እርሱ አስቀድሞ ስለወደደን እግዚአብሔርን እንወደዋለን (1ኛ ዮሐ. 4፥19፤ 2ኛ ቆሮ. 5፥14-15)።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ መገኘታችን እግዚአብሔር እኛን እንዲመራንና በእኛም አማካይነት እንዲሠራ ይረዳዋል። ለጸሎታችንም መልስ እንድናገኝ እምነትን ይሰጠናል፤ ስለ እርሱ የሰጠነው ምስክርነት ውጤቱ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሲሆን በተናገረው ነገር ጸንተን እውነተኞች ሆነን እንድንቆም እምነት ይሰጠናል።

እግዚአብሔርን የበለጠ በወደድነው ቁጥር ለሌሎች ሰዎች ስለ እርሱ በይበልጥ መናገር እንፈልጋለን።

ለ. በሰዎች ላይ ያለን ሁናቴ

ዓላማ፡- በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ውስጥ የተመለከቱትን አራት ሁናቴዎች ገልጻችሁ ለማስረዳት እንድትችሉ ነው።

እነዚህን ሁኔታዎች በራሳችሁ ሕይወት ካመዛዘናችኋቸው በኋላ ደካማ የሆኑ ዝንባሌዎቻችሁን በትምህርቱ መሠረት አጠናክሯቸው። በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ላይ ትክክለኛ ዓላማ ካለን፤

1. ባልዳኑት፥

2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉት ሰዎች እና

3. በአዲስ አማኞች ላይ የሚኖረን አመለካከት የተስተካከለ ይሆናል።

1. ካልዳኑት ሰዎች አንጻር የሚኖረን አመለካከት

በዚህ ዓለም ውስጥ ታላቁ የወንጌል አስፋፊ የሆነው ኢየሱስ በታላቅ ሕዝብ ተከብቦ ይመላለስ ነበር። ብዙዎቹ የተማሩና የተከበሩ ሕዝቦች ሲሆኑ፣ አንዳንዶች ደግሞ የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ፣ ደግሞም ብዙ ስደተኞች፥ ለማኞች፥ ሌቦችና አመንዝሮች ነበሩ። የሃይማኖት መሪዎች በንቀት ሕዝቡን ይመለከቱት ነበር። ከኃጢአተኞች ጋር ይበላል ብለው ኢየሱስን ከሰሱት፣ ኢየሱስ ግን ወዳጃቸው ነበር፣ ሁሉንም ይወዳቸው ነበር። ኢየሱስ ወንጌልን ሄደው የሚሰብኩ 12 ሐዋርያት ነበሩት። እውነተኛው መልእክት ነበራቸው፣ ነገር ግን ፍቅር ነበራቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ አይነግረንም። ዳሩ ግን በቂ ፍቅር ስላልነበራቸው ጌታ ስለ አንድ የጠፋ በግ ታሪክ አስተማራቸው፣ ሉቃስ 15ን አንብቡ። በዚህ ውስጥ የምታዩዋቸው አራቱ የፍቅር መታወቂያዎች ምን ምን ናቸው?

ሀ. ፍቅር የእያንዳንዱን ግለሰብ ክቡርነት ያመለክታል።

ለ. ፍቅር ለጠፉት ሰዎች ይጨነቃል።

ሐ. ፍቅር የጠፉትን ሰዎች በመፈለግ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

መ. ፍቅር የጠፋው በተገኘ ጊዜ ይደሰታል።

በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ተፈላጊነት ያለው ፍቅር ለእያንዳንዱ ግለሰብ የሚሆን እውነተኛ ፍቅር እንጂ፥ ለሕዝብ በአጠቃላይ የሚዘረጋ ፍቅር አይደለም። ኢየሱስ ለኃጢአተኞች ስላለው ፍቅር ብቻ አልተናገረም፣ በጎቹን ለመመለስ ወደዚህ ዓለም መጣ፣ ነፍሳትን ለማዳን ሕይወቱን አጣ፣ ነገር ግን ሕይወቱን የሰጠው በፈቃዱ ነበር፣ አሁንም ዛሬ በእኛ ውስጥ ይኖራል። እርሱ ሌሎቹን እንደሚመለከታቸው እኛም ሌሎችን ልንመለከታቸው እንችላለን (ሉቃ. 19፡10)።

2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት ሰዎች ያለን አመለካከት (ገላ. 6፡10)

የወንጌል ማስፋፋት ሥራ በተባበረ ኃይል የሚሠራ ተግባር ነው። ድሪም ለጠፋባት ሴትና በግ ለጠፋበት ሰው የተሰጡትን ምሳሌዎች አስተውሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ስጦታዎች ያላቸው ሰዎች አሉ፣ እነዚህንም ሰዎችና የተሰጣቸውን የተለያዩ ችሎታዎች እንድንወድና እንድናከብርላቸው ያስፈልጋል። ሰዎችን መውደድ በቤተ

ክርስቲያን ውስጥ ከእነርሱ ጋር በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ተባብረን ለመሥራት እንድንችል ደስታን ይሰጠናል። ፍቅር በእያንዳንዱ ሰው ሥራ እንድንደሰት ያደርገናል እንጂ በሌሎች ጥረት እኛ ብቻ እንድንመሰገን አያደርግም። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የጠፉ ሰዎች አሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያደጉ አንዳንዶች ይኖራሉ፤ ከእነዚህ ሰዎች አንጻር የእኛ አመለካከት በነቃፊነት መገኘት ይገባዋል? የክርስቶስ ፍቅር እነዚህን የመሳሰሉ መንፈሳዊ ችግር ያለባቸውን ሰዎች እንድንረዳቸውና ከእነርሱ ጋር ተግባቢ እንድንሆን ይረዳናል።

### 3. ለአዲስ አማኞች የሚኖረን አመለካከት

ለአዲስ አማኝ ያለን አመለካከት አማኙን ወደ ቤተ ክርስቲያን አንድነትና ወደ እግዚአብሔር አገልግሎት የሚያቀርበው ወይም ወደ ኃጢአት የሚመልሰው ሊሆን ይችላል። አባት ለአባካኙ ልጁ የነበረው አስተያየት እኛም ለአዲስ አማኞች ሊኖረን ይገባል፤ የእኛ የተፈጥሮ ፍቅር ብቻ ነፍሳትን ለማዳን ብቁ ሠራተኞች ሊያደርገን አይችልም፤ ነገር ግን ልባችንን ወደ እግዚአብሔር ብንከፍት የእርሱ ፍቅር የሕይወታችን መመሪያ ይሆናል። በሕይወታችን ውስጥ የጠፉትን ሰዎች ፈልጎ ለማግኘት የሚያስችል መመሪያና ኃይል ሊሰጠን ይችላል።

### ሐ. ለራሳችን ያለን አመለካከት

ዓላማ፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ መልካም አስተሳሰብ እንዲኖራችሁ ለማድረግ ነው። ይኸውም በእግዚአብሔርና በሰዎች ፍቅር ላይ በጥሩ ሁኔታ የተመዛዘነ ፍቅር ሊሆን ይገባል። በውስጣችን የእግዚአብሔር ፍቅር ካለ ለራሳችን መልካም አስተያየት እንዲኖረን ይረዳናል። በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ያለንንም ድርሻ ያስረዳናል፤ በእኛና በሥራችን ላይ ያለን አመለካከት ተቀባይነት፥ ትሕትናና ትጋት ያለው መሆኑን ለማየት መጣር አለብን።

#### 1. ራስን መቀበል

ራሳችንን አሁን ባለንበት ሁናቴና እግዚአብሔርም በዕቅዱ ውስጥ እኛን በመረጠን ስፍራ እንዳለን አድርገን መቀበል አለብን። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ ውስጥ ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል እንደሆኑ ይናገራል። ጆሮ ዓይን አይሆንም፤ እግዚአብሔር ለአንድ ሥራ እንደመደበውና እርሱ ላቀደለት ዓላማ የተመረጠ መሆኑን መገንዘብ አለበት። ሌላውን ሰው ለመምሰል አትሞክሩ፤ ራሳችሁን ሁኑ።

ራስን መቀበል ማለት ውሱን መሆናችንን ከማስረዳቱም ሌላ፥ ስለ ክርስቶስ ምን መሥራት እንደምንችልም ያስተምረናል። እግዚአብሔርን መውደድና ማመን በአንድ ሰው ውስጥ የሚገኙትን መልካም ችሎታዎች ገልጸው የሚያሳዩ ናቸው። እግዚአብሔር ወዶናል፤ የእርሱም መልእክተኞች እንድንሆን መርጦናል፤ በእርሱም ስም ለማስተማር ስንወጣ የእርሱን ሥልጣን እንቀበላለን፤ ራሳችንን ስንቀበልና ደካማነታችንን ለእርሱ ስናቀርብለት እርሱ እንድንሆን የሚፈልገውን ነገር ሆነን እንገኛለን።

ሌሎች ክርስቲያኖች እንደሆኑት እናንተም ለመመስከር ወይም ለመናገር ባለመቻላችሁ ተስፋ የቆረጣችሁበት ወይም ያዘናችሁበት ጊዜ የለም? አሁን በምትገኙበት በታ ታዝናላችሁ? ይህን ጸሎት ጸልዩ። «ጌታ ሆይ፥ ባለሁበት ሁኔታ ራሴን እቀበለዋለሁ፤ በእኔ ውስጥ የምጠላውን የደካማነት ጠባይ ወደ አንተ መልሼ አቀርባለሁ። አንተ የምትሰጠውን ኃይል ለመቀበል ያስችለኛል፤ በየቀኑ ድል ለማድረግ ወደ አንተ እንድመለከት እርዳኝ። ከክርስቶስ አካልም አንዱ ክፍል እንድሆን ስላበቃኸኝ አመሰግንሃለሁ። ለእኔም አንድ የተወሰነ ዕቅድ እንዳለህ በሚገባ አውቃለሁ። አንተ የሰጠኸኝን ስጦታዎችና ችሎታዎች ሁሉ በሚገባ እንድጠቀምባቸው እርዳኝ።»

2. ትሕትና

ራስን መቀበል ማለት ራስን ከፍ ማድረግ ማለት አይደለም፤ ከትሕትናም ጋር መዋሃድ ይኖርበታል። ኩራት ለብዙዎቹ የእግዚአብሔር ሠራተኞች የውድቀት ምክንያት ሆኗል፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ችግሮችን ፈጥሯል (ማቴ. 20፡26–28 አንብቡ)።

ብዙዎች ወደ እምነት የተመለሱት ብዙ ሁኔታዎች በሕይወታቸው ውስጥ ከተፈራረቁ በኋላ ነው።

ይኸውም በጸሎት፥ በምሳሌዎች፥ በምስክርነት፥ በሥነ ጽሑፎች፥ በማስተማር፥ በመስበክና በወንጌል ዝማሬዎች ነው። ስለዚህ አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ በመመለሳችን ልንኮራ አይገባም። ምንጊዜም የእኛ የማስተማር ዘዴ የተሻለ፥ የሌሎቹ ግን አነስተኛ እንደሆነ አድርገን ማሰብ አይገባንም። እያንዳንዱ ሰው የራሱ ድርሻ አለው፤ እግዚአብሔር ስለሰጠን የሥራ ድርሻ እናመስግነው። ሌሎቹም ያላቸውን የሥራ ድርሻ እንወቅላቸው፤ በሥራቸውም ውስጥ እናበረታታቸው (1ኛ ቆር. 5፡3–9፤ ሮሜ 12፡3–5 አንብቡ)።

3. ማነቃቃት

ሥራችንን በመነቃቃት እንሠራዋለን? እግዚአብሔር የሥራ አጋሮቹ እንድንሆን መርጦናል፤ መንፈስ ቅዱስም በእኛ ውስጥ ሊኖር መጥቷል፤ የእርሱንም ሥራ እንድንሠራ ኃይል ሰጥቶናል፤ የእርሱ መልእክተኞች ለመሆን በመብቃታችንና በመመረጣችን ክቡር ነን። እግዚአብሔር ሌላ ሰው ሊሠራው የማይችለውን ልዩ ሥራ ሰጥቶናል፤ የእርሱም ሥራ ከሥራዎቹ ሁሉ የበለጠ እጅግ ከፍተኛ ነው። እርሱ መርጦናል፤ እንድንፈጽመው ያስችለናል። ሥራውን በመነቃቃት ልንፈጽመው ይገባናል። እግዚአብሔር በሥራው ውስጥ ደስታን ይሰጠን። ቆላ. 3፡23፤ ሮሜ 12፡11 አንብቡ።

## 2. የፍቅር ግፊት

ዓላማ፡- ወንጌል የማሠራጨትን ግዴታዎች ከመዘንን በኋላ በይበልጥ ልንወጣቸው የምንችለው እንዴት እንደሆነ ለማስረዳት ነው።

በውስጣችን ያለው ምኞት፥ አሳብና ስሜት ወደ ሥራ ይገፋፉናል። በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ለማከናወን የምትፈልጉት ተግባር ምንድን ነው? ይህንንስ ለምን መረጣችሁ? የምናቀርባቸውን ምክንያቶች ለእግዚአብሔር የሚሰጡት ጠቃሚነት ይወስናቸዋል።

| | |
|---|---|
| የተሳሳቱ ግፊቶች | የተሳሳቱ ሥራዎች |
| ትክክለኛ ግፊቶች | ትክክለኛ ሥራዎች |
| ደካማ ግፊቶች | ደካማ ሥራዎች |
| ጠንካራና ትክክለኛ ግፊቶች | ጠንካራ ሥራዎች |

እኛን በውስጣችን ለአገልግሎት የሚገፋፋን አሳብ ካለን አመለካከት ጋር የሚያድግ ነው፤ እንደ ሁኔታውም ከእግዚአብሔር፥ ከሰዎችና ከእኛም ጋር የተያያዘ ነው።

ራሳችንን ለማስደሰት የምናደርገው ጥረት እግዚአብሔርን ወይም ሰዎችን ላያስደስት ይችላል። በውስጣችን እርስ በርሳቸው የሚቃወሙ አሳቦች ሊኖሩን ይችላሉ ማለት ነው፤ ስለዚህም የትኛው በበለጠ እንደሚጠቅም መለየት አለብን።

እርስ በርሳቸው የሚቃወሙ ግፊቶች ከዚህ በታች ለምሳሌ ያህል ቀርበዋል፡-

1. እግዚአብሔርን የመታዘዝና የማስደሰት ምኞት፥
2. ጎረቤቶችን የመርዳት ምኞት፥
3. የራስን ማንነት የመጠበቅ ፍላጎት።

ከእነዚህ መካከል ሥራችንን የሚመራው የትኛው ነው? ትክክለኛውን ምርጫ እንዴት መለየት እንችላለን? እግዚአብሔርንና ሰውን በበለጠ ስንወድ ትክክለኛውን ለመምረጥ ይቀለናል። በዚህ ዓለም ውስጥ የፍቅር ግፊት ወደር የሌለው ኃይል ነው። ፍቅር የእኛን ስሜቶች ወደ ፍጹም ስምምነት ሲያደርሳቸው የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ከፍተኛ ተደማጭነት ይኖረዋል።

ሀ. የእግዚአብሔር ትእዛዝ

ዓላማ፡- ወንጌልን ስለ ማስፋፋት ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር የተያያዙትን ሦስት ግፊቶች ዘርዝራችሁ ለማስረዳት እንድትችሉ ነው።

- እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መመኘት
- የእግዚአብሔር የሆነ ነገር ሁሉ እንዲሳካ መመኘት
- እግዚአብሔርን ለማስደሰት መመኘት።

1. እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መመኘት

ክርስቶስን እንደ አዳኛችን ስንቀበለው እርሱን እንደ ጌታችን አድርገን ወስደነዋል ማለት ነው። ራሳችንን በእርሱ ትእዛዛት ሥር ማድረጋችንም ነው፤ የወንጌልን ማስፋፋት ሥራ የምናጠናበት አንዱ ዓላማ ይህ ነው። ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን በሰጣት ትእዛዛት እናንተም እንዳላችሁ ታውቃላችሁ።

ሀ. ፍቅር ራሱን ለመግለጽ መንገድ ይፈልጋል። እኛ ለእርሱ ያለንን ፍቅር ስለመግለጽ ኢየሱስ የተናገረው ምንድን ነው? ዮሐ. 14፡15 አንብቡ።

ለ. ፍቅራችንን ለክርስቶስ የምንገልጽለት እንዴት ነው? ማቴ. 28፡19-20፤ ማር. 16፡15፤ የሐዋ. 1፡8።

ሐ. ሐዋርያት እንዳይሰብኩ ሲታዘዙ መስበካቸውን እንዳያቋርጡ ያደረጋቸው ምክንያት ምን ነበር? የሐዋ. 4፡13-20 እንዲሁም የሐዋ. 5፡27-29 አንብቡ።

2. የእግዚአብሔር የሆነው ነገር ሁሉ እንዲሳካ መመኘት

አንድን ሰው በበለጠ የወደድነው እንደሆነ ሥራው ሁሉ እንዲቃናለት እንመኝለታለን፤ የእርሱ ጉዳይ ሁሉ እንዲቃናለት ማድረግ የምንችለውን ሁሉ እናደርግለታለን። ክርስቶስ የዚህ ዓላማ ትክክለኛ ገዢ እንደሆነ እናውቃለን፤ ስለዚህም «መንግሥትህ ትምጣ፥ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን» ብለን

እንጸልያለን (ማቴ. 6፡10)። እንዲሁም «ኢየሱስ ሆይ ና» እንላለን፤ (ራእይ 22፡20)። ነገር ግን እርሱ ከመምጣቱ በፊት የምንሠራው ሥራ ይኖረናል (ማቴ. 24፡14 አንብቡ)።

3. እግዚአብሔርን ለማስደሰት መመኘት

እግዚአብሔርን ለማስደሰት መመኘት እርሱ እኛ እንድንሠራ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ለመሥራት ንቁዎች ያደርገናል። ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሥራ ቅድሚያ እንድንሰጥ ይነግረናል። ከዚያ በኋላ የሚያስፈልጋችሁን ነገር ሁሉ እርሱ ያስብበታል።

ለ. ከሕዝቡ ጋር የተያያዙ ግፊቶች

ዓላማ፡- በፍቅር ላይ ስለ ተመሠረተ የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ጉዳይ ሁለት ሰዎች ሊኖራቸው የሚችለውን የተለያየ ግፊት ዘርዝረን ለማስረዳት እንድንችል ነው።

1. ሰዎችን ለመርዳት መመኘት

2. የእግዚአብሔር መንግሥት እንድትመጣ መመኘት

3. ሰዎችን ለመርዳት መመኘት

ሰዎችን ስንወድ ልንረዳቸው እንፈልጋለን። አንድ ክርስቲያን ወንድም በሚቃጠል ቤት ውስጥ ቢሆን እርሱን ለመርዳትና ለማዳን የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን። በዙሪያችን ለሚገኙት ሰዎች ምን እናደርግላቸዋለን? (ዮሐ. 14፡6፤ የሐዋ. 4፡12 አንብቡ)። ኢየሱስ ስለ ተሰበሰበው ብዙ ሕዝብ ምን ተሰማው? (ማቴ. 9፡35-37)። አንተስ ምን ይሰማሃል?

2. የእግዚአብሔር መንግሥት እንድትመጣ መመኘት

የእግዚአብሔር መንግሥት ሦስት ባሕርያት ምን ምንድን ናቸው? ሮሜ 14፡17።

ሐ. ከራሳችን ጋር የተያያዙ ግፊቶች

ዓላማ፡- ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ ላይ ስንሰማራ ትክክለኛውን መንገድ ለመያዝ የሚረዱንን ሦስት ጠንካራ የተፈጥሮ ግዴታዎች ለማስረዳት እንድንችል ነው።

ሰው ሁሉ ሥራ እንዲሠራ የሚገፋፉ የተፈጥሮ ፍላጎቶች አሉት። እነዚህም በእግዚአብሔርና በሰዎች ፍቅር የተመጣጠኑ ካልሆኑ ራስ ወዳድና ትዕቢተኛ ያደርጉናል። እግዚአብሔር እነዚህን ምኞቶች እርሱን ለማገልገል እንድንጠቀምባቸው ይፈልጋል። በእኛ ውስጥ

የሚገኙ ሦስቱ ጠንካራ ፍላጎቶች የሚከተሉት ናቸው፡- ሥራው እንዲሳካ መመኘት፥ ጓደኝነት መሻትና ሥራው ግቡን እንዲመታ መጣር።

1. ሥራው እንዲሳካና ለተግባራችንም ዋጋ ለማግኘት መመኘት

ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ ዋጋና ግላዊ ደስታ ለማግኘት እንመኛለን? አዎ። ነገር ግን ዓላማቸው ትክክለኛ እንዲሆን ያስፈልጋል፤ ይኸውም ምድራዊውን ሽልማት ሳይሆን ዘላለማዊውን ሽልማት ማለት ነው። ኢየሱስ ዋጋውን ለማግኘት በቀራኒዮ መስቀል ላይ ሰብአዊ ምኞቱን በመስጠት የሠራው እንዴት ነው? (ዕብ. 12፡2 አንብቡ)።

እግዚአብሔር በፍቅሩ ለእኛ ያዘጋጀልንን ዋንኛ ዘላለማዊ ዕቅድ እንመለከታለን? አዎ። እግዚአብሔርን ያስደስተዋል (1ኛ ቆሮ. 3፡8-9)።

በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ላይ የምናገኘው ዋጋ አሁን እግዚአብሔርን በማገልገል ላይ ሳለን የምንቀበለው ደስታ ነው። ወደፊትም በሰማይ የሚገኝ ዋጋ አለ (ዕብ. 12፡2፤ ማቴ. 6፡2፤ ዳን. 12፡3 አንብቡ)።

የክርስቶስ አካል እንደ መሆናችን መጠን በአንድነት እየጸለይን በኅብረት እንሠራለን፤ ይኸውም በዓለም ውስጥ በየትኛውም ክፍል ቢሆን የሚገኘው ድል የእኛ ነው። ሌሎች ክርስቲያን ሠራተኞች እኛ ከምንሠራው የበለጠ ሠርተው ቢሳካላቸው አንቀናባቸውም፤ ነገር ግን እንደሰታለን። እግዚአብሔር ድካማችንን ሲባርክልን ምን ያህል እንደሰት ይሆን?

ለራሳቸው ክብርና ጥቅም እንዲሆን በመመኘት የሚሠሩ ክርስቲያን ሠራተኞች አጋጥመዋችሁ ያውቃሉ? ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አንድ ክርስቲያን ሠራተኛ ሊጠነቀቅባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ናቸው።

ሀ. የዳኑ ሰዎችን ቁጥር ማጋነን

ለ. ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝ ሥራ መመኘት

ሐ. ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያኑ ታማኝ በመሆን ፈንታ ሰውን ለማስደሰት የሚደረግ ስብከት

መ. በታወቁና በታላላቅ ሰዎች ዘንድ ታዋቂነትን ለማግኘት መመኘት

ሠ. ለክርስቶስ ሳይሆን ሰዎችን ለራስ ክብር ማሳመን

ረ. ሌሎች ሰዎች አገልግሎታቸውን እንዲያዳብሩ ከመርዳት ይልቅ ሁሉን ለራስ መመኘት

ሰ. ዓለማዊ ንብረትን ለማግኘት እጅግ መጨነቅ።

2. ጓደኝነትን መመኘት

ሁላችንም ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር ለመሆን እንፈልጋለን፤ የምንወዳቸውም ሰዎች ከእኛ ጋር በሰማይ እንዲኖሩም እንመኛለን። በተለይም የክርስቶስን ጓደኝነት እንሻለን። አዲስ ወይም ወጣት ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሽማግሌዎች ጋር ለእግዚአብሔር ሥራ አገልግሎት የሚሰማሩበት ጊዜ የለም? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ መሪ ጓደኛና ረዳት በማጣት ሲወድቅ አልተመለከታችሁም? ወጣት ሰዎች ከነባር ክርስቲያኖች ጓደኝነት በማጣታቸው ቤተ ክርስቲያንን ጥለው ሲሄዱ አልተመለከታችሁም? ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያቱን ሁለት ሁለቱን እያደረገ የላካቸው ለምን ይመስላችኋል? (ማር. 6:7፤ ማቴ. 18:19–20 አንብቡ)።

3. ሥራው ግቡን እንዲመታ

ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ ዓላማውን ለመፈጸም ፈጣን ፍላጎት አለው። የዚህ ትውልድ ታላቅ ጭንቀት ለሕይወቱ ማቀድ ነው። እግዚአብሔር እኛ እንድንፈጽመው ለፈጠረን ሥራ ብቁ ሆነን ስንገኝ እንደሰታለን። (ኤፌ. 2:10 አንብቡ)። ስለ ራስ ገልጾ ማስረዳት የሕይወት ሕግ ነው። ተከታዮች ተከታዮችን ይፈጥራሉ፤ የወይን ግንድ የወይን ዘለላን ያፈራል። እንዲሁ የኢየሱስ ሕይወት በአማኙ ውስጥ በፍቅርና በብርሃን ራሱን ይገልጻል። ብርሃን ከማብራት አያቋርጥም። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ መንፈሳዊ ፍሬን ያፈራል። በአዲሱ ተፈጥሮ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር ራሱን እየገለጸ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ይመልሳል።

## 3. ለፍቅር የምንገባው ግዴታ

ዓላማ፡– የወንጌልን ሥራ ለማስፋፋት ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንድንሰጥና በፍቅር ላይ በተመሠረተ ቃል ኪዳን በታማኝነት እንድንሠራ ለማስተማር ነው።

* ቃል ኪዳን ማለት አንድን ሥራ ወይም ውሳኔ ለመፈጸም ቃል መግባት ማለት ነው።

* ግዴታ ማለት አንድ ዓይነት ሥራ ለመፈጸም ራሳችንን መለየት ማለት ነው።

አንድ ነገር ለማን ወይም ለምን እንደምንሠራ ማወቅ በቂ አይደለም። አንድን ነገር ለምን መሥራትና በከፍተኛ ትጋትም ለምን መፈጸም እንደምንሻ ማወቅ በቂ አይደለም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እንድንፈጽመው ለመረጠን ሥራ በትክክለኛው መንገድ ለመሥራት እንድንችል ራሳችንን ለእግዚአብሔር ቃል ማስገዛትና የውዴታ ግዴታ መግባት ይኖርብናል።

ለወንጌል ሥራ መስፋፋት ቃል ኪዳን መግባት የሚጀመረው ለእግዚአብሔር በማያወላውል ሁኔታ ግዴታ ስንገባ ነው፤ ይኸውም በእኛ ውስጥ እንደ ወደደ እንዲሠራ ስንፈቅድለት ነው።

ይህስ ቃል ኪዳን የሚሠራው መቼ ነው? ቃል ኪዳን መግባቱ ከተፈጸመ በኋላ ለክርስቶስ ብለን የገባንበትን ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሥራት እንዳለብን ራሳችንን ማስታወስ ይኖርብናል። ሌላ የተለየ ሥራ ወይም ለመሥራት አስቸጋሪ ነገር ቢገጥመንም እንኳ ለእርሱ ስንል በየቀኑ ሥራችንን ማከናወን ይኖርብናል።

ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ በዕቅድ የሚካሄድ ብርቱ ሥራ ነው። በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 እንደምናነበው ገንዘቧ የጠፋባት ሴት ቤቷን ሁሉ በመጥረግ ፈለገች እንጂ ዝም ብላ በመቀመጥ አላለቀሰችም። በተሰጠን በእግዚአብሔር ሥራ አገልግሎት ፈንታ ማናቸውንም ዓይነት ሌላ ሥራ እንድንሠራ የሚገባ ሆኖ ሲገኝ ፈቃደኞች እንሆናለን? ወይስ መስበክ ወይም ማስተማር ብቻ እንጂ ቤተ ክርስቲያንን አልጠርግም፤ ወገኖችን አልጎበኝም፤ ወዘተ... እንላለን?

ሙሉ ጊዜውን በእግዚአብሔር ሥራ ላይ የሚያውል ወንጌላዊ ወይም ክርስቲያን ሠራተኛ እንደ ወዝ አደር ወይም እንደ ቢሮ ሠራተኛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሰዓት ለመሥራት ፈቃደኛ መሆን አለበት።

ሥራችሁን በደስታ፥ በመነቃቃት፥ በጸሎት፥ በትጋትና በእምነት ትሠራላችሁ? እግዚአብሔር እንዲመራችሁና እንዲሠራባችሁ ትፈቅዱለታላችሁ? በመጨረሻም ለማንኛውም ሥራ የምንገባውን ቃል ኪዳን በሚገባ እንድንፈጽም የሚያደርገን ሥራው የቱን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ መገንዘባችን ነው።

አገልግሎታችንና ጥረታችን በሚከተለው ሁኔታ ከተካሄደ እርካታ ይሰጠናል።

ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር ያለን አንድነት (ሮሜ 12፡1-2)

ለ. በሰዎች ፊት ታማኞች ሆነን መገኘት (1ኛ ቆሮ. 4፡1-2)

ሐ. የአገልግሎታችንን ጊዜ አለማባከን (ኤፌ. 5፡15-16)።

አንዳንድ ሰዎች ዘላለማዊ ደኅንነትን ሊያገኙ የሚችሉት እኛ በታማኝነት ሥራችንን በሠራንበት መጠን ነው። ሰዎችን ሁሉ በያሉበት ልናገኛቸው አንችልም፤ ነገር ግን አንዳንዶቹን ልናገኛቸው እንችላለን። ሰው ሁሉ ትምህርታችንን ላይቀበለው ይችላል፤ ነገር ግን እኛ ድርሻችንን ከሠራን አንዳንዶቹ ሊቀበሉን ይችላሉ። ዘላለማዊ ኑሮአቸው ውሳኔ የሚያገኘው በእኛ ጸሎት፥ ምስክርነትና እርዳታ ከእግዚአብሔርና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ወንጌልን በማስፋፋት በምናደርገው ትብብር ነው።

ጊዜያችን አጭር ስለሆነ የእኛ ሥራ ጠቃሚ ነው። ምናልባት ለረጅም ጊዜ ላንሠራ እንችል ይሆናል፤ የመከር ሰዓት በደረሰ ጊዜ ፍሬው ሲበስል መታጨድ ይኖርበታል። አንድን ነገር እንዳይጠፋ በየቀኑ የተቻለንን ያህል በሚገባ እንሠራለን። የሥራችን ጠቃሚነት ምን ያህል እንደሆነ እናውቃለን? እንዴት አድርገን ልናሻሽለው እንችላለን?

## ጥያቄዎች

1. ለእግዚአብሔር፥ ለሰዎችና ለራሳችን ያለንን ፍቅር እንዴት ልናጠናክረው እንችላለን?
2. ራሳችንን መቀበል ጠቃሚ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ ትክክለኛ ያልሆኑት ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?
4. ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ መልካም የሆኑት ምክንያቶችስ የትኞቹ ናቸው?
5. አንድ ክርስቲያን ሥራው እንዲከናወንለት በማሰብ ሲሠራ አደጋ የሚያስከትሉት ነገሮች የትኞቹ ናቸው?
6. ወንጌልን ማስፋፋት ማለት መስበክና ማስተማር ማለት ብቻ ነው? ሕይወታችን ተሳትፎ የሚያደርግባቸው ሌሎቹ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
7. በወንጌል ተሳትፎ የእኛ ድርሻ የቱ ነው? የእግዚአብሔርስ?

# ትምህርት 3

## መንፈስ ቅዱስና ቃሉ

1. መንፈስ ቅዱስ በቃሉ አማካይነት ሲሠራ
   - እግዚአብሔርን ይገልጻል።
   - ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ መሠረታዊ መሣሪያ ይሆናል።
2. በክርስቲያኖች አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ ሲሠራ
   - ለመመስከር የሚሆን ኃይል ይሰጣል።
   - መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት ያስችላል።
   - መንፈሳዊ ስጦታዎች ይሰጣል።

### 1. መንፈስ ቅዱስ በቃሉ አማካይነት ሲሠራ

እግዚአብሔር ራሱንና ቃሉን ከብርሃን ጋር ያነጻጽራቸዋል። በሉቃስ 15፡8 ላይ ድሪም ስለጠፋባት ሴት እናነባለን። ሴቲቱ ምን አደረገች? በመጀመሪያ መብራቷን አበራች። እኛ የምንፈልጋቸው ሰዎች በጥርጥር፥ ባለማመን፥ እርግጠኛ ባለመሆን፥ ራስን በመውደድ፥ በፍርሃትና ተስፋ በመቁረጥ ጨለማ ውስጥ ናቸው። የራሳችን ጥበብ የጠፉትን ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሊመራቸው አይችልም፤ ብርሃን ያስፈልገናል፤ ይኸውም የመንፈስ ቅዱስ ብርሃንና የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቤተ ክርስቲያን መብራቷን ልታበራ ይገባታል።

ሀ. እግዚአብሔርን ይገልጻል

ዓላማ፦ በእውነት ለመሥራትና በቃሉ አማካይነት በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ ውስጥ ክርስቶስን ሊገልጽ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ለመግለጽ ነው።

እያንዳንዱ ክርስቲያን እንደ አንድ መብራት ነው። ሆኖም መብራት ሁሉ የኃይል ምንጭ ያስፈልገዋል። አንድ መብራት ብርሃን ከመስጠቱ በፊት ዘይት ወይም ኤሌክትሪክ ማግኘት ይኖርበታል። እግዚአብሔር ለክርስቲያን በመንፈሱና በቃሉ አማካይነት ኃይል ይሰጠዋል። ቃሉ በራሱ ብቻ በቂ አይሆንም። እንደዚሁም መንፈስ በራሱ በቂ አይሆንም፤ የመንፈስና የቃሉ ውህደት የወንጌልን ብርሃን በእኛ አማካይነት ለሌሎች እንዲበራ ያደርገዋል [ማቴ. 5፡14፥ 16፤ መዝ. (18)፡28፤ (119)፡130፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡6 አንብቡ]።

መንፈስ ቅዱስ በቃሉ አማካይነት ለሕዝቡ ይናገራል። የእግዚአብሔርን መልእክት በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ለሌሎች እንዲያስተላልፉ ሰዎችን አነሣሥቷቸዋል። ሰዎች ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ከመቀበላቸው በፊት እርሱ ማን እንደሆነና ለእነርሱም ምን እንዳደረገላቸው፣ እርሱን ማገልገል ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ በቃሉ የተገኘውን ጠቅላላ የእውነትን መገለጽ እናስተምራለን። ጠቅላላ የወንጌል መገለጽ ትምህርት በቂ አይደለም። ባለንበት ሁኔታ እውነትን በተግባር ለማዋል የሚገፋፋን ይህ ነው።

ሰዎች ላለባቸው ግላዊ ችግር መፍትሔ የሚሆን ነገር ከእግዚአብሔር ቃል እየጠቀስን ልናስረዳቸው ይገባል። ሰዎች ያለባቸውን ችግርና መፍትሔ የሚያውቅና የሚረዳቸው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ እንደ ሥርዓት ሆኖ የተዘጋጀ አንድ ደንብ የለም። ብዙ ጊዜ የተወሰነ የአሠራር ዘዴም ሊዘጋጅ ያልቻለበት ምክንያት ይኸው ነው። ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገው መንፈሳዊ ነገር የተወሳሰበ ከመሆኑ የተነሣ ይህንኑ ለማስወገድ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ይመጣል። ከመልእክቱ ውስጥ ልንመርጠው የሚገባንን ቃል ይመራናል። በምናስተምርበትም ጊዜ አዲስ አሳብና ሌላም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ያቀርብልናል፤ ይኸውም እኛ ልንጠቀምበት አስቀድመን ያላቀድነውን ሊሆን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ ሰዎች እውነትን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፤ በችግራቸውም ውስጥ እንዲጠቀሙበት ያደርጋል። እንዲያምኑ እምነትን ይሰጣቸዋል። እውነትንም ተቀብለው በእርሱ እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል። ከዚህ በኋላ የተሰጠው ተስፋ የተፈጸመ መሆኑን ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል። ክርስቲያን እንደ መሆናችን መጠን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የምናነብበውን ሁሉ ወዲያውኑ ልንረዳቸው አንችልም። ሌሎች ሰዎች ይረዱናል። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ትርጉሙን ብሩህ አድርጎ ይገልጽልናል።

በጸሎት ተሞልተን መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ በቃሉ አማካይነት እግዚአብሔር ለእኛ እንደሚናገረንና እውነትንም ሕያው አድርጎ እንደሚገልጽልን መጠበቅ ይገባናል። እግዚአብሔር ለሌሎች እንድናካፍል የሚፈልገውን መልእክት እንድናስተምር ይመራናል።

ለ. ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ መሠረታዊ መሣሪያ ይሆናል

<u>ዓላማ</u>፡- የወንጌል ማስፋፋትን ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በቃሉ አማካይነት መሥራት እንድንችል ለማስረዳት ነው።

ብርቱ የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ለመፈጸም በእግዚአብሔር ቃል ላይ መተማመን አለብን፤ ኃይሉን ማወቅና መልእክቱንም ማስተላለፍ

ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ የተጻፈና ከእርሱም የመነጨ መሆኑን በመጠራጠራቸው ብዙ ሰባኪዎች ደፍረው ስለ እርሱ አይናገሩም።

መንፈስ ቅዱስ እምነትን ለመፍጠር በቃሉ አማካይነት ይሠራል። የእግዚአብሔርን ቃል የበለጠ ባነበብንና ባሰላሰልን ቁጥር ቃሉን በሥልጣን ለመስበክ የበለጠ እምነት እናገኛለን። ሌሎች በእምነት ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ከፈለግን ለእምነታቸው መሣሪያ እንዲሆን ቃሉን ልንሰጣቸው ይገባናል፤ ይህ ለመዳንና ለመንፈሳዊ ዕድገት ተፈላጊ ነው። ሐዋርያት ሕይወታቸውን እስከ መሠዋት ድረስ እምነታቸውን እንዲያካፍሉ ያደረጋቸው በእግዚአብሔር ቃል ላይ የነበራቸው እምነት ነው።

ቃሉን መስበክና ማስተማር እንዲሁም ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነብቡ ማበረታታት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? (ሮሜ 1፡17፥ 10፡7፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡23፤ ኢሳ. 55፡10–11 አንብቡ)። ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ መሠረታዊ መሣሪያ የሆነን መጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ ሰዎች እርሱን እንዲያነብቡ ወይም እንዲሰሙ ማበረታታት ይገባናል፤ የራሳችንንም አሳብ ከማስተማር ይልቅ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር፥ መስበክና መመስከር አለብን።

ኢትዮጵያዊውን አዛዥ እንዲገናኘው ፊልጶስን የወሰደው መንፈስ ቅዱስ አዛዡም ደግሞ ስለ ኢየሱስ የተጻፈውን ትንቢት እንዲያነብ መራው፤ እንዲሁም ወደ ጥያቄውና ወደ መልሱ አድርሶታል (የሐዋ. 8፡28–40 ተመልከቱ)። ከመልሱ አንዱ ክፍል የተሰጠው ፊልጶስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ባገኘው እውቀት ነው (ቁ. 35 ተመልከቱ)።

ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን እናያለን። በየቀኑም የምናጠናበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። ቃሉንም የበለጠ በተረዳነው መጠን መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውን ጥቅስ በሚያስፈልገን ጊዜ ለአእምሮአችን ለማቅረብ ይቀለዋል።

## 2. በክርስቲያኖች አማካይነት መንፈስ ቅዱስ ሲሠራ

መንፈስ ቅዱስ በቃሉ ብቻ ሳይሆን በእኛም አማካይነት ይሠራል። ይህንን የሚሠራውስ እንዴት ነው?

1. ለመመስከር እንድንችል ኃይልን በመስጠት፤
2. መንፈሳዊ ፍሬን በመስጠት፤
3. በመንፈሳዊ ስጦታዎች አማካይነት።

ሀ. ለመመስከር እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሰጣል

ዓላማ፡- እኛ ሕይወታችንን ለእርሱ እንድንከፍትና እርሱም በእኛ አማካይነት በነጻነት እንዲሠራ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ኃይል ለማሳየት ነው።

ኢየሱስ ሐዋርያት የወንጌል ማስፋፋት ሥራን ብቻቸውን እንደማይፈጽሙት ያውቅ ነበር። ስለ ወንጌል ማስፋፋት ሥራ የተሰጠውን ትርጉም አስታውሱ።

ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ ማለት እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች የማዳኑን ዜና ለመስጠት በሕዝቡ አማካይነት ሲሠራ ማለት ነው። እግዚአብሔር ፍቅሩን ሲያፈስ፥ ለጸሎት ጥያቄዎች መልስ ሲሰጥና ወንጌል እውነት መሆኑን ለሕዝቡ ሲያስረዳ የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአተኞች እንዲያምኑ እምነትን ሲሰጥና በንስሐም እንዲመለሱ ፈቃደኞች ሲያደርጋቸው ማለት ነው።

ስለዚህ ኢየሱስ ተከታዮቹን ለመስበክ ከመውጣታቸው በፊት መንፈስ ቅዱስ እስኪመጣ እንዲጠብቁ አስጠነቀቃቸው (የሐዋ. 1፡4-5፤ 8።)

እግዚአብሔር በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ዛሬም መንፈስ ቅዱስን ይልክላቸዋል። በትምህርታችን፥ በእውቀታችን፥ በችሎታችን አንመካም። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላን ራሳችንን ለእርሱ መተው ሲኖርብን በምንናገረውና በምናደርገው ነገር ሁሉ ለእርሱ መሪነቱን እንዲወስድ መፍቀድ ይኖርብናል። እግዚአብሔር ከእኛ ሊገኝ የማይችለውን ብርታት፥ ጥበብና ኃይል ይሰጠናል።

በጴጥሮስ ላይ የደረሰውን ሁኔታ ተመልከቱ። ፍርሃት ጌታውን እንዲክድ አደረገው፤ ነገር ግን ከጰንጤቆስጤ (ከበዓለ ኀምሳ) በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታላቅ ምስክር ሊሆን ችሏል። በዚያው ቀን በእርሱ ምስክርነት 3000 ሰዎች ክርስቶስን ተቀበሉ። በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ የእግዚአብሔር ቃል ይናገረናል (ኤፌ. 5፡18)።

ክርስቶስንና መንፈስ ቅዱስን በመቀበል አንድ ክርስቲያን ወደፊት ሊያገኝ የሚገባውን ኃይል ወዲያውኑ በማከታተል ሊያገኝ አይችልም። መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ችግር የሚያፈልገውን ኃይል ለማግኘት እንድንችል ይረዳናል። መከራ ሲመጣ ስለ ክርስቶስ እንዳንናገር እንታዘዛለን። ምናልባት እንፈራ ይሆናል፤ ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር በጸሎት እየቀረብን ቃሉን በምናነብበት ጊዜ ከእኛ ላይ ያለውን ፍርሃት አስወግዶ ብርታትንና እምነትን ይሰጠናል። (1ኛ ቆሮ. 2፡1-5 አንብቡ)።

እያንዳንዱ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላ ይችላል። ሕይወታችንንና ፈቃዳችንን በተውንለት መጠን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላን ይችላል። በራስ ፈቃድ በፍርሃት ወይም በሌላ በማናቸውም ዓይነት ኃጢአት የተሞላውን ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ሊሞላው አይችልም። መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር ስንፈቅድለት ኃይል በሕይወታችን ውስጥ ይሞላል።

ለ. መንፈሳዊ ፍሬ (ቆላስይስ 1፡10)

ዓላማ፡- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ የቱን ያህል ጠቃሚ እንደሆነና ይህንንም ለማስፋፋት እንዲረዳችሁ እምነታችሁን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ እንድትችሉ ለማስተማር ነው።

እኛ በምንናገረውና በሁኔታችን መጠን መንፈስ ቅዱስ የወንጌልን እውነት ለሕዝቡ ያሳምናል።

ልብሶቹና እጆቹ ስለ ቆሸሹበት አንድ የሳሙና ነጋዴ ምን ታስባላችሁ? ደግሞም ክርስቶስ ስለሚሰጠው አዲስ ሕይወት እየተናገረ የእርሱ ሕይወት ግን በራስ ወዳድነትና በኃጢአት ስለ ተሞላ ሰውስ ምን ይሰማችኋል? ዓለም ውሳኔ አድርጎ ከመቀበሉ በፊት የወንጌልን ኃይል በእኛ ሕይወት ውስጥ አስቀድሞ ማየት ይገባዋል።

የአንድ ዛፍ ፍሬ የዛፉን ዓይነት እንደሚመሰክር የእኛም ሥራ የእግዚአብሔርን መኖርና ፍቅር እውነተኛነት ማረጋገጥ ይኖርበታል። የምንፈተንበት ምክንያት ይህ ነው፤ የማያምኑ ወዳጆች እንድንበሳጭ ወይም እንድንወድቅ ሊፈትኑን ይችላሉ። ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይግባውና ኢየሱስ እኛን መርጦ መንፈሱን በእኛ ውስጥ ስላኖረ ፈተናውን ልንቋቋመው እንችላለን! የእርሱም ታላቁ መልእክት መስበክ፥ ማስተማርና መመስከር ብቻ ሳይሆን ፍሬ ማፍራትም ጭምር ነው። (ዮሐ. 15፡16 አንብቡ)። ይህንንም እኛ በራሳችን ልናፈራ አንችልም፤ ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስንተባበርና እኛንም እንዲቆጣጠረን ስንፈቅደለት በእኛ ይህንኑ ሊያደርግ ይችላል (ገላ. 5፡22-25 አንብቡ።)

ኢየሱስ በመንፈሱ በእኛ ውስጥ ይኖራል። የቸርነቱን፤ የፍቅሩን፤ የደስታውን ብርሃን ሰዎች በእኛ ውስጥ በተመለከቱ ጊዜ በክርስቶስ እውነተኛነትና ኃይል ይተማመኑበታል።

ሐ. መንፈሳዊ ስጦታዎች

ዓላማ፡- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የቱን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑና በወንጌል ማስፋፋት ሥራ እግዚአብሔር በእናንተ አማካይነት

እንዲሠራ እንድትተማመኑበት ለማስተማር ነው (ኤፌ. 4፡11፤ ሮሜ 12፡6–8፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡8–10፤ 28–30)።

መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወትና በአገልግሎቱ አማካይነት ይሠራል። ስጦታዎችንና ችሎታዎችን በመስጠት እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር ሊሠራ የሚፈልገውን ሥራ እንዲያከሂድ ያደርገዋል።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ልናስታውስ የሚገባን አንድ ነገር አለ። ስጦታዎችን ለራሳቸው ብቻ እንዲጠቀሙባቸው ለክርስቲያኖች አልተሰጡም፤ ነገር ግን በአማኙ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ የሚሠራባቸው መንገዶች ናቸው። (1ኛ ቆሮ. 12፡1–31 አንብቡ)። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደሆነች ጳውሎስ ይናገራል። እያንዳንዱ የአካላችን ክፍል የተለየ ሥራ እንደሚሠራ ሁሉ እንደዚሁም በክርስቶስ አካል ውስጥ የሆነው አባል የሚፈጽመው የተለየ ሥራ አለው።

እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አንዳንድ ጥቅሶችን እንድንረዳ ማስተዋል ይሰጠናል። በሚገጥሙን ነገሮች ሁሉ ላይ ልናደርገው የሚገባንን ጥበብ ይገልጽልናል፤ መንፈስ ቅዱስ አንዳንድ ነገሮች ምናልባት ከሰይጣን መሆናቸውን ለመለየት እንድንችልና ተቋቁመንም እንድናሸንፋቸው ለይቶ የማወቅን መንፈስ ይሰጠናል።

እግዚአብሔር ለሙሴና ለሰባዎቹ ሽማግሌዎች የመሪነት ስጦታ ሰጣቸው። የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠራ ለታዘዘው ለባስልኤል እንዴት አድርጎ መሥራት እንደሚችል ስጦታዎችን ሰጠው (ዘጸ. 31፡3 አንብቡ)።

ጳውሎስ ለሕዝቡ አገልግሎት የበለጠ ጠቃሚ ይሆናሉ ብሎ ያስተማራቸው ስጦታዎች የትኞቹ ናቸው? (1ኛ ቆሮ. 14፡1–5 አንብቡ)። «ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን፥ ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ።» ይህ የትንቢት ስጦታ የእግዚአብሔርን ቃል ወይም መልእክት ማሳወቅ ማለት ሲሆን፥ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ረዳትና አጽናኝ ይሆናል። በቋንቋዎች መናገር የሚረዳው ያንኑ የሚናገረውን ሰው ብቻ ነው።

መንፈስ ቅዱስ እንድንሠራ በሰጠን ሥራ በእያንዳንዱ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ሊመራንና ሊረዳን ይፈልጋል፤ ነገር ግን እኛ ሰዎችን እያማን፥ እያማረርን፥ የብልግናም ወሬ እየተጫወትን መንፈስ ቅዱስ በእኛ አማካይነት የእግዚአብሔርን መልእክት እንዲሰጥ እንጠብቃለን? በንግግራችን ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት

ምላሳችንን ባሠለጠንነው መጠን ስለ እርሱ መናገር ቀላል ይሆንልናል (ማቴ. 12፡34 አንብቡ)።

የኃይል ስጦታዎች (እምነት፥ ማዳንና ታምራቶች) ከጸሎት ጋር በቅርብ የተያያዙ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ለመቀበል የማይቻል መስሎ የሚታየውን ነገር እንድንጸልይበት እምነት ይሰጠናል። በታሪክ ሂደት ወስጥ እግዚአብሔር ለጸሎት ታምራታዊ መልሶች እየሰጠ ለሕዝቡ የእርሱን ኃይልና ፍቅር በመግለጽ ለማሳመን ተጠቅሞበታል።

የጠፉትን የምንመልስ እኛ አይደለንም፤ ነገር ግን ለእርሱ ራሳቸውን በሰጡ አማኞች ሕይወትና አንደበት ተጠቅሞ ራሱ ክርስቶስ ነፍሳትን ይመልሳቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. ወንጌልን ለማስፋፋት መሠረታዊ የሆነው የክርስቲያን መሣሪያ ምንድን ነው?
2. መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች አማካይነት የሚጠቀምባቸው ሦስቱ መንገዶች ምን ምን ናቸው?
3. የክርስቲያን ሕይወትና ምሳሌነት ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ በጣም ጠቃሚ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?
4. የወንጌልን ማስፋፋት ሥራ ለማካሄድ የሚሠራበት አንድ የተወሰነ ዘዴ ያልኖረበት ምክንያት ምንድን ነው?
5. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ዓላማ ምንድን ነው?

# ትምህርት 4

# የጸሎት ኃይል

1. በምንጸልይበት ጊዜ ምን ምን ይፈጸማል?
   - እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ይሠራል።
   - እግዚአብሔር በሌሎች ውስጥ ይሠራል።
   - እግዚአብሔር ተመቻችተው በሚገኙ ነገሮች ውስጥ ይሠራል።
2. ለምን እንጸልያለን?
   - ለመነቃቃትና ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ፥
   - ለግላዊ ችግር፥
   - ለአገልጋዮች።
3. መጸለይ የሚገባን እንዴት ነው?
   - ስለ ሁሉ ነገር ለእግዚአብሔር በመንገር፥
   - በኢየሱስ ስም በመጠየቅ፥
   - እግዚአብሔርን በማመንና በማመስገን፥
   - በትጋት፥
   - ለብቻና ከሌሎችም ጋር በመሆን፥
   - መንፈስ ቅዱስ በጸሎታችን እንዲረዳን በመጠየቅ።

## 1. በምንጸልይበት ጊዜ ምን ይፈጸማል?

የጸሎትን ምሥጢር ማንም ሰው ሊያውቀው አይችልም። ነገር ግን ስለሚሰጠው ውጤት እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን! ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ በሥራው ውስጥ በዚህ መንገድ ድርሻ እንዲኖረን ለምን አደረገ? እርሱን በሚያስደስቱ ሥራዎች ልጆቹ ተካፋይ እንድንሆንና ልንፈጽመው የሰጠንንም ሥራ በትክክለኛው መንገድ ለመፈጸም ከእርሱ ጋር እንድንወያይበት ነው። ድል ለሰጠንና ለጸሎታችንም መልስ ላስገኘልን ለእርሱ ምስጋና ስናቀርብለት በጸሎታችንም ይደሰታል። በፍቅርና በወንድማማችነት በአንድነት ተያይዘን በጸሎት እንድንተማመን አድርጎናል። እርሱን በመምሰል እንድናድግና ከእርሱም ጋር ጊዜያችንን እንድንጠቀምበት ይፈቅዳል? ለሰዎች ስለ ችግራቸው በምንጸልይበት ጊዜ በእነርሱ ፍቅር ሊሞላን

ይፈቅዳል። አንዳችን ለሌላው በምንጸልይበት ጊዜ እንደ ልጆቹ አንዱ ሊያደርገን ይፈልጋል። የሆነው ሆኖ በማናቸውም ምክንያት ሲሆን እኛ በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥና በሌሎች ወስጥ እንዲሁም ተመቻችተው በሚያገኛቸው ጊዜዎች ውስጥ እንደሚሠራ እናውቃለን።

ሀ. ስንጸልይ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ይሠራል

ዓላማ፡- በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ጸሎትና ምስጋና ምን ውጤት እንደሚያስገኝ ለማስረዳት ነው።

በምንጸልይበትና እግዚአብሔርን በምናመሰግንበት ጊዜ ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ፍቅርና ለሰው መራራትን መንፈስ ቅዱስ ይሰጠናል።

ሰው ማማትና በሰዎች ላይ ነቀፌታን መፈለግ እንዲድኑ የምንፈልጋቸው ወዳጆቻችን ወይም ሌሎች ሰዎች ክርስቶስን እንዳይቀበሉ ሊከለክላቸው ይችላል። ይልቁንም እግዚአብሔር ስለ ወዳጆቻችንና ለእነርሱ ሊያደርግላቸው ስለሚፈቅደው ነገር ሁሉ እናመስግነው።

እግዚአብሔር ኢዮብን ያዳነው መቼ ነው? እርሱ ስለ ወዳጆቹ በጸለየበት ጊዜ ነበር (ኢዮብ 42፡10)። በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በዙሪያችን ያሉትን ሰዎች ችግር እንድናይ ይረዳናል፤ ምስክርነት ወደ ምንሰጣቸው ሰዎች ይመራናል።

እንዲሁም ምስጋና አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔርን በእምነት በምናመሰግንበት ጊዜ እርሱ እምነታችንን ያጠነክርልናል፤ ያለብንንም ጥርጥር ያስወግድልናል፤ ፍርሃታችንንም ድል ያደርገዋል። ጸሎታችሁ ባዶ ቃላት ብቻ እንደሆነ አስባችሁ አታውቁም? ወይም እግዚአብሔር ከእናንተ የራቀና የማይሰማ መስሎ ተሰምቷችሁ አያውቅም? አንዳንድ ጊዜ ሁላችንም እንዲህ ያለ ስሜት ይሰማናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን ብናመሰግነው እምነታችን ይታደስልናል።

ለ. በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች ውስጥ ይሠራል (1ኛ ሳሙ. 12፡23)።

ዓላማ፡- ወደ እግዚአብሔር በምንጸልይበትና በምናመሰግንበት ጊዜ እግዚአብሔር የሚሠራባቸውን መንገዶች ለመግለጽና ይህንን እውነት በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ አግብተን ለመጠቀም ሌሎችም እንዲሠሩበት ለማበረታታት ነው።

እግዚአብሔር እንዲባርከን በጸሎት ማስቸገር አያስፈልገንም። እንዲሁም ነፍሳትን ለማዳን ፈቃዱ ነው ወይ ብለን መጠየቅ አያስፈልገንም። ይህን ሁሉ ሊያደርግ እርሱ ፈቃዱና ዕቅዱ ሆኗል። ነገር ግን ስንጸልይ ከዚህ ከፍሎ ይሰጠናል። ስለ ሰዎች በምንጸልይበትና እግዚአብሔርንም ስለ ጸሎታችን መልስ በምናመሰግንበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር ይገልጽላቸዋል፤ ይኸውም በብዙ መንገድ አንድ አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸው ያሳያቸዋል። ስለ እግዚአብሔር ለሰዎች ከመናገራችን በፊት አስቀድመን ስለ ሰዎች ለእግዚአብሔር እንናገር። እኛ ከመዳናችን በፊት ለእኛ ለእያንዳንዳችን አንድ ሰው ጸልዮልናል። ስለ እናንተ የጸለየው ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ?

**ሐ. በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር በተመቻቹ ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ ይሠራል (የሐዋ. 12፡5–10፥ 16፡22–34)።**


ዓላማ፡– የወንጌልን ማስፋፋት ሥራ ያሰናከሉ የነበሩ ነገሮች በጸሎትና በምሥጋና እንዴት በመልካም ነገሮች ሊለወጡ እንደቻሉ ምሳሌዎች ለመስጠት ነው።

ሰይጣን የወንጌልን ማስፋፋት ሥራ ለማሰናከል የተቻለውን ያህል ይጥራል። ነገር ግን እግዚአብሔር እርሱ እኛን ድል አድርጎ ለመጠቀም የሚፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ወደ በረከት ይለውጣቸዋል።

እያንዳንዱ የችግር ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት አድርጎ እንደሚመልስ የምናይበት አጋጣሚ ነው። ሰዎች ሊሠሩ የማይችሏቸውን ነገሮች እግዚአብሔር በተለይ እየሠራ ይታወቅበታል። መጸለይ፥ ማመስገን፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አምኖ መሥራትና እግዚአብሔርንም መጠባበቅ የማይቻለውን ነገር ይሠራል።

## 2. ለምን እንጸልያለን?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታላላቆቹ የእግዚአብሔር ሰዎች የጸሎት ሰዎች ነበሩ። ለወንጌል ማስፋፋት ሥራ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን ከእነርሱ ልንማር እንችላለን።




## ሀ. ተሐድሶና ወንጌልን የማስፋፋት ሥራ

<u>ዓላማ</u>፡- ተሐድሶን ከወንጌል ማስፋፋት ጋር አያይዘን በጸሎት ስለሚደረገው መነቃቃት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠውን ምሳሌ መከተል እንድንችል ለማስተማር ነው።

ዳንኤል፥ ዕዝራና ኤርምያስ የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ስለ ሕዝባቸው ኃጢአት ራሳቸውን ኃጢአተኞች አድርገው በመቁጠር አለቀሱ። በእነርሱም ጸሎት አማካይነት እግዚአብሔር መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲፈጠር አደረገ፤ ሕዝቡም ከምርኮ ተመልሰው ተሐድሶ አካሄዱ።

መነቃቃት ማለት እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚፈጽመው ሥራ ማለት ነው። የማያምኑትን ወደ ክርስቶስ የሚያመጣቸው የክርስቲያኖች መነቃቃት ነው። በመነቃቃት ጊዜ ክርስቲያኖች በኃጢአታቸው ይጸጸታሉ። ለእግዚአብሔርም በመታዘዝ ራሳቸውን ይሰጣሉ፤ ራሳቸውንም በሚሰጡበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ስለ ጠፉት ሰዎች እንዲያስቡ በፍቅር ይሞላቸዋል። ስለዚህም ስለ ጠፉት ሰዎች መዳን መጸለይና መሥራት ይጀምራሉ (2ኛ ዜና. 7፡14 አንብቡ፤ በቃላችሁም አጥኑት)።

ዕንባቆም ምን ብሎ ጸለየ? (ዕንባ. 3፡2)። ይህ ለእኛ ጸሎት ይሁን። ይህንን ጥቅስ አንብባችሁ አጥኑት።




በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገው መነቃቃት ኃጢአተኞችን ወደ ክርስቶስ እንዳቀረባቸው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እናያለን። እንደዚሁም ጸሎት በማነቃቃት ሥራ ውስጥ ሁሉ ትልቅ ድርሻ አለው። ሌሊቱን ሁሉ ለሌሎች የሚጸልዩ ሰዎች ነበሩ። በአንዳንድ የማነቃቃት ሥራዎች ውስጥ ስብከት የያዘው ትንሹን ክፍል ነበር። መጸለይ ብቻ የምትችሉ ከሆነ ይህ ለመነቃቃት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ አስታውሱ። መነቃቃት ማለት ምን ማለት ነው? መነቃቃት ማለት መንፈሳዊ ንቃትና የእግዚአብሔር ሕዝብ መታደስ ማለት ነው።

ለ. ግላዊ ችግሮች

<u>ዓላማ</u>፡- የምትጸልዩባቸውን ጊዜያት ሁሉ ለምትመሰክሩላቸው ሰዎች ችግር ለማዋል እንድትችሉ ለማስተማር ነው።

በሐዋ. 1፡14፥ 2፡41-47 ጸሎትና ምስጋና ለቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ ዋናውን ቦታ የያዘ እንደነበር እናነብባለን። ቃሉን የማጥናታቸውና የአንድነታቸው፥ የጸሎትና የምስጋናቸው ውጤት በአንድ ቀን 3000 ሰዎችን በእምነት ወደ ክርስቶስ አመጣ።

የሐዋ. ሥራ 4፡23-31 ጴጥሮስና ዮሐንስ የአይሁድን ሹማምንት ትእዛዝ በነገሯቸው ጊዜ ክርስቲያኖቹ ምን ብለው ጸለዩ? በጸለዩስ ጊዜ ምን ደረሰ? ቤተ ክርስቲያንን በማቋቋም ረገድ ጳውሎስ መለኮታዊ ችሎታ ተሰጥቶት ነበር፤ ይኸውም ለእያንዳንዱ ግላዊ አግኝ የማያቋርጥ ጸሎት ማድረግ ነበር። በሉቃስ 15 ውስጥ ኢየሱስ የእያንዳንዱን ሰው ዋጋ አጉልቶ ሲናገር ለእያንዳንዳቸው እንደሚያስብላቸው ይገልጻል። ስለዚህ «ጌታ ሆይ የታመሙትን ፈውስ፥ ነፍሳትን አድን፤ ምእመናንንም በመንፈስ ቅዱስ ሙላቸው» ብቻ ብለን መጸለይ አይበቃም። በአካባቢያችን ያሉትን ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚያስፈልጋቸው አውቀን ለእያንዳንዳቸው የተለየ ችግርና የተወሳሰበ ጉዳይ ልንጸልይላቸው ይገባል።

ለሰዎች ችግር ከልብ ማሰብ ብዙ ጊዜ ለመመስከርና ከእርሱ ወይም ከእርሷ ጋር አብሮ ለመጸለይ መንገድ ይከፍታል። የጸሎትን መልስ ማግኘት እምነት ይሰጣል። ብዙውን ጊዜ ክርስቶስን ወደ መቀበል ይመራቸዋል። ይህ በመቶ በሚቆጠሩ ጎረቤቶችና በየቤታቸው በሚሰበሰቡ ቡድኖች ሕይወት ውስጥ ሲፈጸም ታይቷል። ሰዎችን በየቤታቸው ሄዶ መጎብኘት ብዙዎች ክርስቶስን እንዲቀበሉ አድርጓቸዋል። አንድ ወንጌላዊ በየቤቱ እየተዘዋወረ ጉብኝት አደረገ፤ «በዚህ ቤት ውስጥ የታመሙ ሰዎች አሉ? ለእነርሱ እንድጸልይላቸው ትፈቅዳላችሁ?» ብሎ ጠየቀ። ቤተሰቡ ይህን በመፍቀዱ ጸለየ፤ እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰማው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወንጌላዊው ያ ሕመምተኛ ሰው እንዴት እንደሆነ ለመጎብኘት ተመልሶ ሄደ። የጸሎቱ መሰማት ያ ቤተሰብ በእግዚአብሔር ፍቅርና ኃይል ላይ እንዲተማመን አደረገ። ከዚህ በኋላ ወንጌልን ለመስማት የተዘጋጁ ሆኑ። ብዙዎች ክርስቶስን ተቀበሉ፤ ወዲያውም ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች።

ሐ. ሠራተኛ

ዓላማ፦ ለምታውቋቸው ክርስቲያን ሠራተኞች አብዝታችሁ እንድትጸልዩና እንዲሁም እግዚአብሔር በበለጠ ሠራተኞችን እንዲልክ እንድትለምኑ ለማስተማር ነው።

አንዲት ሴት በምትኖርበት ከተማ ውስጥ የወንጌል መስበክ አስፈላጊ መሆኑ ተሰማት። እርሷ ግን ልትጸልይ እንጂ ልትሰብክ አልቻለችም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን እንዲያቋቁምና ሰዎችን እንዲያድን ለብዙ ቀናት እየጾመች ጸለየች። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር አንድ ወንጌላዊ እዚያ ሄዶ እንዲሰብክ ላከ። ብዙዎች በክርስቶስ አመኑ፤ ጠንካራም ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች።

አንዳንድ ጊዜ ብዙ ሰዎች ወንጌልን መስማት እንዳለባቸውና ጥቂት የወንጌል ሠራተኞች ብቻ እንዳሉ በምታስቡበት ጊዜ ብርቱ ጭንቀት አይሰማችሁም? በሉቃስ 10፡2 ላይ ስለዚህ ነገር ኢየሱስ ምን እንድናደርግ ይነግረናል?

በአንዳንድ መንደር ወይም ከተማ ስላሉ ሰዎች ታስባላችሁ? ምናልባትም ስለ ራሳችሁ መንደር ሊሆን ይችላል። ስለ እነዚህ ችግሮች በየቀኑ በመጸለይና ሌሎችም ስለ እነዚሁ ችግሮች እንዲጸልዩ ትጠይቃላችሁ?

ቤተ ክርስቲያናችሁና በአካባቢያችሁ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ ሌሎች ወንጌልን እንዲሰሙ የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ? እያንዳንዳቸውንም እግዚአብሔር ሠራተኛ እንዲያደርጋቸው የእናንተ ጸሎት ያስፈልጋቸዋል? ብዙ ሠራተኞች እንዲልክ መጸለይ ብቻ አይበቃንም። ነገር ግን በመሥራት ላይ ላሉ ሠራተኞችም የመጸለይ ኃላፊነት አለብን። ይህንንም ከጳውሎስ ልንማር እንችላለን። እነርሱን ወደ ክርስቶስ ሊመራቸው ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ አገልግሎት እነርሱም እንዲጸልዩለት ጠይቋቸዋል (2ኛ ተሰ. 3፡1 አንብቡ)። ለወንጌላውያን፥ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ ለሰንበት ትምህርት ቤት መምህራን፥ እንዲሁም ለሌሎች ሰባኪያን እንጸልያለን?

## 3. መጸለይ የሚገባን እንዴት ነው?


ዓላማ፦ ስድስቱን የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ደንቦች ሥራ ላይ በማዋል ተደማጭነት ያለው የጸሎትና የምሥጋና አገልግሎት እንዲስፋፋና ሌሎችም እንዲበረታቱ ለማድረግ ነው። ስለ ጸሎትና ስለ ምሥጋና ብዙ መጻሕፍትን ልናነብብ እንችላለን። የመጽሐፍ ቅዱስን ጸሎትና ተስፋዎች በማጥናት ብዙ ርዳታ ለማግኘት እንችላለን።

ለጸሎታቸው መልስ ያገኙትን ሰዎች ሁኔታ ስንሰማ ያበረታታናል። በጸሎት አማካይነት ብዙ ልንማር እንችላለን። ለጸሎት ውጤት የሚያስገኙ ስድስት ደንቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

ሀ. ስለ ሁሉ ነገር ለእግዚአብሔር ተናገሩ

ሁለት ልጆች ያሉትን አንድ ሰው እንመልከት። አንደኛው ልጅ ስለማናቸውም ነገር ከአባቱ ጋር ይወያያል፤ እንዲሁም አባቱ የሚለውን ነገር ሁሉ ያዳምጣል። ሁለተኛው ልጅ ግን አንዳንድ ነገር ለመጠየቅ ካልሆነ በቀር ከአባቱ ጋር አይወያይም፤ አባቱም በሚናገርበት ጊዜ አያዳምጥም። እናንተ ይህን አባት ብትሆኑ ኖሮ ከእነዚህ ከሁለቱ ልጆች ከማንኛው ጋር ለመሥራት ትመርጣላችሁ?

እውነተኞች ሆነን ስለማናቸውም ነገር ከእግዚአብሔር ጋር እንነጋገር። እርሱ ከእኛ ለመስማት የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን እኛ የምናስበውንና ስሜታችንን ሁሉ ለእርሱ እንንገረው። ኃጢአታችንን ሁሉ እየተናዘዝን ይቅርታ እንጠይቅ። ከእግዚአብሔር ልንሰውራቸው አንችልም። በልዩ የጸሎት ቋንቋና ባማሩ ቃላት እግዚአብሔርና ሰውን ለማሞኘት አንሞክር። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው በምንናገረው ነገር እውነተኞች ሆነን እንድንገኝ ነው።




ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ የጊዜ ማሳለፊያ ውይይት ሳይሆን ቁም ነገር አዘል ጭውውት ነው። በምንጸልይበት ጊዜ እናድምጥ፤ የዕለት ተግባራችንንም በምንፈጽምበት ጊዜ ማድመጣችንን እንቀጥል። እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ ሊሰጥ፥ ሊመራንና እምነትም ሊሰጠን ይፈልጋል። መልእክቱንና የመንፈስ ቅዱስንም ኃይል ሊሰጠን ይፈልጋል።

ለ. በኢየሱስ ስም ጸልዩ

ይህም ማለት በምንጸልይበት ጊዜ «በኢየሱስ ስም» ብቻ እንድንል አይደለም። የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንንና ከክርስቶስ ጋር

አንድነት እንዳለን ስለምናውቅ ስለዚህም በእርሱ ኃይልና ሥልጣን መሠረት መጠየቅ እንችላለን (ዮሐ. 14፡13–14)።

ሐ. እግዚአብሔርን እመኑና አመስግኑ

በምንጸልይበት ጊዜ የምንጠይቀውን ነገር እንደምናገኝ ማመን ይኖርብናል። እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ማመን ያለብን ሲሆን፥ ራሱን እግዚአብሔርንም ልናምነው ይገባል። የሥራው ባልደረቦች እንድንሆን ጠርቶናል። የራሱንም ድርሻ እንደሚፈጽም ልናምን ይገባል (ያዕ. 1፡6፤ ማር. 9፡23 አንብቡ)። በእምነት እየጸለይን እግዚአብሔር ለሚያደርገው ነገር ሁሉ እናመስግነው።

መ. የተጋቻሁ ሁኑ

መትጋት ማለት ምንም እንኳ መሰናክልና ተቃዋሚ ቢበዛ የተጀመረውን ሥራ በትጋት መቀጠል ማለት ነው። እግዚአብሔር ለአንድ ዓይነት ነገር ተስፋ ሰጥቶ እንደሆነ ይህ የእርሱ ፈቃድ መሆኑን እናውቃለን፤ መልሱንም እንዲሰጠን እየጸለይን እናመስግነው። ቤተ ክርስቲያንን ሊያንቀሳቅና ኃጢአተኞችን ሊያድን የእርሱ ፈቃድ እንደሆነ እናውቃለን። ስለዚህ ለወዳጆቻችን መጸለያችንን እንቀጥል። የጸሎታችንን መልስ ወዲያውኑ ባላገኘን ጊዜ ተስፋ ልንቆርጥ አይገባንም (ቆላ. 4፡2 አንብቡ)።

ሠ. ለብቻችሁና ከሌሎች ጋር ጸልዩ

የእኛ ምሳሌ የሆነው ኢየሱስ ከአባቱ ጋር በጸሎት ብዙ ጊዜ ያሳልፍ ነበር። ነገር ግን ከሐዋርያትም ጋር አብሮ በጉባኤ ይጸልይ ነበር። ሐዋርያት በአንድነት እንዲጸልዩና ስለሚጸልዩበትም ነገር እንዲስማሙ አስተማራቸው። በተባበረ ጸሎት ውስጥ ታላቅ ኃይል አለ (ማቴ. 18፡19–20፤ የሐዋ. 2፡41፥ 3፡1 አንብቡ)።

ረ. መንፈስ ቅዱስ በጸሎታችሁ እንዲረዳችሁ ጠይቁ

መንፈስ ቅዱስ እኛ እስከፈቀድንለት ድረስ እንድንጸልይ ሊረዳን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ስለ አንዳንድ ሰዎች ወይም ስለ አንዳንድ ችግሮች እንድናስብ ሲያደርገን፥ ለእነርሱ ስንጸልይ እናገኛለን። እያንዳንዱ ሰው ያለበትን ችግር ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ያውቀዋል። የእኛንና የምንጸልይላቸውን ሰዎች ችግሮች ያውቃል። የሚያስፈልገውን ነገር እኛ አናውቅም፤ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ስለ እኛ እንዲቃትትልንና ችግሩን እንዲገልጽልን ያስፈልጋል።

## ጥያቄዎች

1. «ያለማቋረጥ መጸለይ» ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል? 1ኛ ተሰ. 5፡17።
2. በምንጸልይበት ጊዜ ማመስገን ለምን ያስፈልጋል?
3. በምንጸልይበት ወቅት እግዚአብሔር የሚሠራው በእነማን ውስጥ ነው?
4. የሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌነት ስለ ጸሎት ምን ያስተምረናል?
5. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመለከቱትን ስድስቱን የጸሎት ደንቦች ከልሱ።

# ትምህርት 5

# ስለ ኃጢአት የቀረበ መልእክት

ኃጢአት ማለት፡-

- የነፍስ በሽታ፥
- እግዚአብሔርን መካድ፥ እና
- በሕይወት ውስጥ የተሳሳተ አቅጣጫን መያዝ ማለት እንደሆነ ለሕዝቡ ንገሩ።

ሰዎች ያለባቸውን ችግር ግለጹላቸው፡-

- ጥፋታቸውን ግለጹላቸው
- የሚገጥማቸውን አደጋ ግለጹላቸው።

## 1. ኃጢአት ምን እንደሆነ ለሕዝቡ ንገሩ

ይህ ትምህርት «የወንጌል ማስፋፋት ሥራ» አንዱ ክፍል ነው።

አንዳንዶቹ ይሰብኩታል፤ አንዳንዶቹ ያስተምሩታል፤ አንዳንዶቹ በውይይት መልክ ያካፍሉታል፤ ነገር ግን መልእክቱ ያው ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መልእክተኛ ቢሆንም፤ ሁላችንም መልእክቱን መማር ይገባናል። በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ኢየሱስን እንደ አዳኝ አድርገን እናቀርበዋለን፤ ነገር ግን አዳኝን የሚፈልግ ማን ነው? በአደጋ ውስጥ ያሉ መሆናቸውንና ራሳቸውን ለማዳን የማይችሉ መሆናቸውን ያወቁ ብቻ ናቸው። አብዛኛው ሕዝብ ለመዳን ያለበትን ችግር አያውቁትም። በመልካም ኑሮ ውስጥ ለመኖር

የሚሞክሩ ብዙ ሰዎች ኃጢአተኞች መሆናቸውን አይረዱትም፤ ምክንያቱም ኃጢአት ምን እንደሆነ ባለማወቃቸው ነው። ስለ ኃጢአት በምናስተምርበትና በምንሰብክበት ጊዜ ኃጢአት ሰዎች የሚሠሩት ብቻ ሳይሆን፥ ከዚያ የበለጠ ታላቅና ጥልቅ እንደሆነ እንገልጻለን።

1. ኃጢአት የነፍስ በሽታ ነው።

2. ኃጢአት እግዚአብሔርን መካድ ነው።

3. ኃጢአት በሕይወት ውስጥ የተሳሳተ አቅጣጫን መያዝ ነው ሲል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል።

ሀ. ኃጢአት የነፍስ በሽታ ነው

<u>ዓላማ</u>፡- እናንተ ካላችሁበት ማኅበር ውስጥ የሚገኘውን የተለመደ የኃጢአት ትርጓሜ ከመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ጋር በማስተያየት ለማነጻጸር ይህንንም እውቀት በጸሎታችሁ፥ በምስክርነታችሁ፥ በትምህርታችሁና በስብከታችሁ ውስጥ እንድትጠቀሙበት ነው።

በማር. 7፡20-23 የተገለጹት ነገሮች ኃጢአት የነፍስ በሽታ ለመሆኑ ምልክት ናቸው።

የነፍሳቸው በሽታ የሆነው ኃጢአት በግልጽ ፈንድቶ ስላልወጣ ብዙ ሰዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ አያውቁትም፤ ይህንንም ሌሎች ሰዎች ሲሠሩት የሚያዩት ነው። ስለ ኃጢአት እግዚአብሔር የሚለውን ቢያውቁ ኖሮ እጅግ አድርገው በጠቀማቸው ነበር። ኃጢአተኛ ሁሉ አዳኝ ያስፈልገዋል (ሮሜ 1፡23-28)።

እግዚአብሔር በኢሳ. 1፡5-6 ውስጥ ኃጢአት ምን እንደሆነ በዝርዝር ይገልጻል። ክፉ አሳቦችንና የተሳሳቱ ስሜቶችን፥ እንዲሁም የተሳሳቱ ሥራዎችን የሚሰጥ ኃጢአት ነው። (ሮሜ 1፡18-32 አንብቡ)። ኃጢአት የሚጀመረው ሆን ብሎ ትክክለኛውን ነገር ከመሥራት በመታቀብ ነው፤ ሰዎች መልካሙን ነገር ከመሥራት ሲታቀቡ ለመሥራት የፈቀዱትን ክፉውን ነገር እንዲሠሩ እግዚአብሔር ይተዋቸዋል፤ ከዚህ በኋላ አንዱ ኃጢአት ሌላውን እንዲቀጥሉ በማድረግ ባሪያ ያደርጋቸዋል።

እነዚህ ጥቅሶች በማናቸውም ማኅበራዊ ኑሮ ወይም ገለልተኛ ሰው ኑሮ ውስጥ ኃጢአት እንዴት እንደሚስፋፋ ይገልጻሉ። ሮሜ 1፡21 የመጀመሪያው እርምጃ ነው። በሕይወታቸው ውስጥ ለእግዚአብሔር የመጀመሪያውን ስፍራ አይሰጡትም፤ እግዚአብሔር ስለሚሰጣቸው

በረከት አያመሰግኑትም፤ ስለ እግዚአብሔር የተሳሳተ አሳብና ስሜት አላቸው።


ኃጢአት እንዴት እንደሚስፋፋ ቁ. 22–23ን አንብባችሁ ተረዱ። በመጨረሻም ሰዎች የሚሠሩት ሥራ ስሕተት እንደሆነ ይረዱታል፤ ነገር ግን ያንኑ በመሥራት ይቀጥላሉ። (ሮሜ 1፡32ን ከያዕቆብ 1፡15 ጋር አወዳድሩት።) የነፍስ በሽታ የማይድን ከሆነ የመጨረሻ ውጤቱ ምን ይሆናል?

እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ውስጥ ወንጀልን፥ የፍርድን ጉድለትና የማኅበራዊ ኑሮን ጥፋት መከላከል የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

ለ. ኃጢአት ማለት እግዚአብሔርን መካድ ነው

ዓላማ፡– በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔርን መካድ ምን እንደሚመስል የሚገልጽና ስለ ኃጢአት የሚያስረዳ ትምህርት በሦስት ዓይነት መልክ የሚገልጽ ሥዕል ሠርታችሁ ማሳየት እንድትችሉ ለማስተማር ነው።

እግዚአብሔር በራሱ አምሳል ፈጥሮናል፤ ስለዚህም ልጆቹ ልንሆን እንችላለን፤ (ዘፍ. 1፡26–27)። አእምሮ፥ ፈቃድና ስሜትን ሰጥቶናል። አካላችን እንደ አንድ ሕንጻ ሆኖ በእርሱም ውስጥ የምንኖር መሆናችንን ጳውሎስ ተናግሯል። በውስጡም ተፈጥሮ፥ አእምሮ፥ ፈቃድና ስሜት አለው።





ስለ አፍአዊ ችግራችንና ስለ አካላችን እግዚአብሔር አስፈላጊውን ነገር ሁሉ አዘጋጅቶልናል። እንደዚሁም ስለ መንፈሳዊ ችግራችን የሚያስፈልገንን አዘጋጅቶልናል። አንድ ሰው ከአካል የበለጠ ተፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር በሰውነታችን ውስጥ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ አዘጋጅቶልናል።

በትክክል መኖር እንድንችል እግዚአብሔር፥


- እውነቱን ለአእምሮአችን
- ፍቅሩን ለስሜት ችግራችን
- የመምረጥ ችሎታን ደግሞ ለፈቃዳችን ሰጥቷል። እነዚህን አስፈላጊ ነገሮች በሕይወታችን ውስጥ ከተቀበልን እግዚአብሔርን በሕይወታችን ዙፋን ላይ እናስቀምጠዋለን፤ መልካምና አስደሳች ኑሮ ለመኖር መንገዱ ይህ ነው።




ፈጣሪ በፍጥረቱ ላይ ለመግዛት ሙሉ ሥልጣን አለው። ሕይወትን የሰጠንና የሚያስፈልገንን ሁሉ ያዘጋጀልን እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ የመጀመሪያውን በታ ለመያዝ ሥልጣን አለው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፈንታ እኛው ራሳችንን ለመግዛት ከወሰንን ይህ ሽፍትነት ሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ የሚመነጩበት መሠረታዊ የኃጢአት መነሻ ይሆናል። በኃጢአት የተሞላ ሰውነት ከእግዚአብሔር ዙፋኑን ነጥቆ ይወስዳል።

1. የእግዚአብሔር እውነቶችን አለማመን
2. ለእግዚአብሔር ፍቅር ግድ የለሽ መሆን
3. በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ መሸፈት።

ኃጢአት እግዚአብሔርን መካድ ነው፤ ይኸውም አእምሮአችንን፥ ፈቃዳችንንና ስሜታችንን ከእግዚአብሔር ይልቅ ለራስ ጥቅም ብቻ ጠብቆ መያዝ ማለት ነው።




ኃጢአት፡- እግዚአብሔርን መካድ ነው

1. እውነትን አለማመን

እግዚአብሔር ስለ አንድ ነገር በሚናገረን ጊዜ ሳናምን ስንቀር ይህ ያለማመን ኃጢአት ይባላል። የሰው ዘር ኃጢአት የጀመረው ከዚህ ነው። ሰይጣን ሔዋንን በእግዚአብሔር እውነት ላይ እንድትጠራጠር አደረጋት (ዘፍ. 3፡1–5 አንብቡ)።

የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ወደ ተሳሳቱ ስሜቶች፥ የተሳሳቱ ስሜቶች ወደ ክፉት ሥራዎች ይመራሉ። እግዚአብሔር ከኃጢአት ተመልሰን ከክርስቶስ ወደተሰጠው የማዳን መንገድ ገብተን በወንጌል እንድናምን ይነግረናል። ከኃጢአት ለመዳን እንድንችል እምነታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማድረግ እንደሚገባን ያሳስበናል። እግዚአብሔር የሚለውን ነገር አለመቀበልና ለመዳን ወደ ሌላ መንገድ መመልከት ኃጢአት ነው፤ ይህ በሙሉ ፈቃደኝነት የሚፈጸም ያለማመን ኃጢአት ነው። የእግዚአብሔርንም እውነት እንዳለመቀበል የሚቆጠር ነው (ዕብ. 2፡2–3 አንብቡ)።

በክርስቶስ የተሰጠው የእግዚአብሔር መንገድ ከኃጢአት ለመዳን ያለው ብቸኛ መንገድ ነው። እውነተኛ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት የሚያጸድቀው ይህ ነው። (ዮሐ. 1፡12፥ 3፡14–16፥ 14፡6 አንብቡ)።

2. ለፍቅር ግድየለሽ መሆን

እግዚአብሔር ፍቅር ነው (1ኛ ዮሐ. 4፡16)። እኛ በምንወድበትና በምንወደድበት ጊዜ ብቻ ስሜታዊ ችግሮች ይፈጠራሉ። እግዚአብሔር ሰዎችን ከራስ ወዳድነት፥ ከፍርሃት፥ ከትዕቢት፥ ከወንጀልና ከጦርነት

ነፃ ሊያወጣቸው የሚችለው ለእነርሱ ያለውን ፍቅር አምነው ሲቀበሉ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጾልናል፤ በዚያም ፍቅር እያንዳንዱን ሕይወት ሊሞላ ይፈልጋል (ሮሜ 5፡5)። አምልኮታችንና ምሥጋናችን እኛ ለእርሱ ያለንን ፍቅር የሚያሳዩ መንገዶች ናቸው። ያለ ፍቅር ለእግዚአብሔር የሚደረግ ሥነ ሥርዓታዊ አምልኮ ሁሉ ባዶ ነው ማለት ይቻላል።

1ኛ ዮሐ. 4፡7–21 አንብቡ። የፍቅሩን መጉደል እንደ ኃጢአት እንቆጥረዋለን? ክርስቶስ በቀራንዮ ላይ ያቀረበልንን የፍቅር ስጦታ ለመቀበል ፈቃደኞች ሆነን ያልተገኘን እንደሆነ እርሱን እንደሰደብነው ይቆጠራል።

3. በባለሥልጣኖች ላይ መሸፈት

እግዚአብሔር የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪና ገዢ እንደመሆኑ መጠን እርሱ የተፈጥሮና የሞራል ሕጎችን፥ እንዲሁም መንፈሳዊ ሕጎችን ለመላው ፍጥረት ጥቅም ሲል ደንግጓል። ፀሐይና ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ ፕላኔቶች ሁሉ ለፈጣሪያቸው ሥልጣን አንገዛም ቢሉ ምን ይደርሳል? የተለመደ ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ።

የሆነው ሆኖ ሰው የእግዚአብሔርን ሥልጣን ንቋል፤ በእግዚአብሔር ሥርዓት ላይ ሸፍቷል፤ የራሱን መንገድ ብቻ ይዞ ይጓዛል። በሌሎች ሰዎች ላይ በግልጽ የምንሠራው ስሕተት ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ እንደሚፈጸም ኃጢአት ሆኖ ይቆጠራል። (1ኛ ዮሐ. 3፡4፤ ያዕ. 4፡17) አንብቡ።

በአፍአዊ ሁኔታዎች ከቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ጋር የተስማማን ሆነን ለመገኘት ስንችል፥ በውስጣችን ግን በእግዚአብሔር ላይ የሸፈትን ሆነን ልንገኝ እንችላለን።

ሐ. ኃጢአት ማለት በሕይወት ውስጥ የተሳሳተ አቅጣጫ መያዝ ማለት ነው።

<u>ዓላማ</u>፡– እናንተ በምትኖሩበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች በሕይወት ውስጥ የተሳሳተ አቅጣጫን ስለመያዝ ሁኔታ ዘርዝራችሁ ማስረዳት እንድትችሉ ለማድረግ ነው።

እግዚአብሔር በራሱ አምሳል የፈጠረን ለአንድ ዓላማ ነው።

ሀ. በዚህ ዓለም ሳለን እግዚአብሔርን እንድንወድና እንድናፈቅር፥

ለ. የዘላለማዊ ክብሩ ተካፋይ እንድንሆን፥

ከዚህ ዕቅድ ውጪ እግዚአብሔርን እንድናከብር የሚመልሰን ወይም የሚከለክለን ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው። ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ የተሳሳተ አቅጣጫን ይይዛሉ፤ ይኸውም በደስታ፥ በኃይል፥ በመታበይ ወይም በዝና ሊሆን ይችላል።

መልካም አቅጣጫዎችም እንኳ ቢሆኑ እግዚአብሔር እኛን የፈጠረበትን ዓላማ ሊሸፍኑ ይችላሉ። የሰዎችን ሥቃይ ማቃለል፥ ለትክክለኛ ፍርድ መሥራት ወይም ሰዎችን ደስ ማሰኘት ሁሉም መልካም ዓላማዎች ሲሆኑ፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር የሆኑት የመጀመሪያውን ቦታ ሊወስዱ ይችላሉ።

በአንድ ባንክ ቤት ውስጥ የባንኩ ሠራተኛ ገንዘብን ያላግባቡ ሲያጠፋ ካየን እንገረማለን፤ ነገር ግን ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕይወት ያለአግባብ ሲጠቀሙ ይታያሉ።

ጻድቅ መሆን ማለት እግዚአብሔር ከሰጠው ትክክለኛ የኑሮ ደረጃ ወይም ዓይነት ላይ ደርሶ መኖር ማለት ነው። ክርስቶስ እዚህ ለመድረስ የሚያስችለንን ብቸኛ መንገድ ይኸውም ጽድቁን እንዲሰጠን መፍቀድ ነው። ብዙ ሰዎች ሌሎች የሚሠሩትን ክፉ ሥራ ስለማይሠሩ እኛ ኃጢአተኞች አይደለንም ይላሉ (2ኛ ቆሮ. 10:2 አንብቡ)። እግዚአብሔር ራሳችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር ማነጻጸር እንደማይገባን ይናገራል። እርሱ የእኛ ደረጃ መለኪያ ስለሆነ እግዚአብሔር የሚቀበለው የክርስቶስን ጽድቅ ብቻ ነው።

መ. ጥፋታቸውን ግለጹላቸው

የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ሰዎች ጥፋታቸው ምን እንደሆነና ስለሚያስፈልጋቸው ይቅርታ ንገሯቸው። ኃጢአትን ማመን ማለት አንድ ሰው በእግዚአብሔር ላይ መሸፈቱን አምኖ መቀበል ማለት ሲሆን፥ ይቅርታም እንደሚያስፈልገው ማወቅ ነው። ከኃጢአት መዳን ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የፈጸመውን አምኖ መቀበል ማለት ሲሆን፥ ይኸውም በመስቀል ላይ ስለ እኛ ኃጢአት የከፈለውን ዋጋ ማለት ነው።

ወደ ክርስቶስ መጥተን ኃጢአተኞች መሆናችንን እንናዘዛለን፤ እንዲሁም እንዲቀበለንና ይቅር እንዲለን እንጠይቀዋለን። ወንጀለኞች፥ ሰካራሞች፥ እንዲሁም ዘማውያን ኃጢአተኞች እንደሆኑ ያውቃሉ። ወደ ክርስቶስ ለመመለስ የሚያስቸግሩ ሰዎች ራሳቸውን ትክክለኞች አድርገው የሚመለከቱት ናቸው። እነርሱ የሚሠሩት መልካሙ ሥራ ከፉውን ሥራ ለማስወገድ የበለጠ ክብደት ያለው ይመስላቸዋል። እግዚአብሔር ግን ጽድቃችን በእርሱ ፊት እንደ

መርገም ጨርቅ የሚቆጠር መሆኑን ይናገራል (ኢሳ. 64፡6 አንብቡ)። እኛን ያዳነን የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት እንጂ ሥራችን አይደለም። (ሮሜ 3፡23-24፤ ቲቶ 3፡5-7 አንብቡ)። ብዙውን ጊዜ እኛ የሠራነውን ስሕተት ሌሎች ሰዎች ከእኛ የበለጠ ሊያዩት ይችላሉ። በፊታችን ላይ አንድ ቆሻሻ ነገር ተለጥፎ ካገኘን ምን እንደምንመስል ለማወቅ በመስተዋት እናያለን። የእግዚአብሔር ቃል እንደ መስተዋት ነው። በእግዚአብሔር የቅድስና መለኪያ ስንመለከት ኃጢአተኞች እንደሆንን እንረዳለን (ያዕ. 1፡21-25 አንብቡ)።

እግዚአብሔር የቃሉን መስተዋት ለሕዝቡ እንድናሳይ ኃላፊነት ሰጥቶናል፤ ስለዚህ ይቅርታ እንደሚያስፈልጋቸው እግዚአብሔር ሊያሳያቸው ይችላል (1ኛ ዮሐ. 1፡8፤ ኢሳ. 64፡6፤ ሮሜ 3፡13፤ ያዕ. 2፡10 አንብቡ)።

አንዲቷ ነጥብ እንኳ ብትሆን የእግዚአብሔርን ሕግ የተላለፈ ሰው ሁሉ በሁሉም ስለ በደለ ኃጢአተኛ ነው። በማቴ. 22፡37-40 የቀረቡት ሁለት ሕጎች ከሁሉ የሚበልጡ መሆናቸውን እግዚአብሔር ተናግሯል። እነርሱም፤

1. እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም አሳብህም ውደድ፤ ይህ ከሁሉ የበለጠና በጣም አስፈላጊ የሆነው ነው።

2. ጎረቤትህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ። ይህን የፈጸመ አንድም ሰው የለም፤ ስለዚህ ሁላችን ኃጢአተኞች ነን።

ሰዎች ኃጢአተኞች መሆናቸውን ሌላ ሰው እንዲያስታውሳቸው አይወዱም። ነቢያትን በድንጋይ ወገሩ፤ ኢየሱስን ሰቀሉ፤ ክርስቲያኖችንም አሳደዱ። የሰዎችን ኃጢአት ለማስረዳት መንፈስ ቅዱስ በቃሉ አማካይነት በውስጣችን ሆኖ ስናስተምር ተቃውሞ ሊገጥመን እንደሚችል ማወቅ ይኖርብናል።

ሰዎች የምንነግራቸውን ነገር አንቀበልም ሲሉ ተስፋ ልንቆርጥ፥ ትዕግሥት ልናጣ ወይም በቁጣ ልንናገር አይገባም። ምናልባት የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወታችን ውስጥ ተገልጾ ለማየት ይፈልጉ ይሆናል፤ ይኸውም ስድብን ይቅር የሚል ፍቅር ማለት ነው።

ከሠራው ስሕተት የተነሣ ማንንም ቢሆን እንደ አለቃ ሆነን ልንከራከረው አይገባም። ስለ ኃጢአት በምንናገርበት ጊዜ የፍቅር፥ የትሕትና፥ ለሰው የማሰብ ሁኔታ በእኛ ላይ እንዲታይ ያስፈልጋል (ኤር. 23፡28-29፤ ዕብ. 4፡12 አንብቡ)። በሰዎች ልብ ውስጥ

የሚሠራው የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ወዳጆቻችንና ጎረቤቶቻችን መጽሐፍ ቅዱስን ከእኛ ጋር እንዲያጠኑ እናበረታታቸው።

ሠ. የሚገጥማቸውን አደጋ እንግለጽላቸው

ዓላማ፡- ኃጢአት የሚያስከትለውን ኃይለኛ መከራና መዳንም የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም ለሕዝብ ማስረዳት እንድንችል ነው።

የምኖርበት ዓለም እግዚአብሔር ባቋቋመለት የተፈጥሮ ሕግ መሠረት በአንድነት ተያይዞ ይኖራል፤ እንደዚሁም የማኅበራዊ ኑሮ ወይም ማንኛውም ሰው እግዚአብሔር በወሰነው የሞራልና የመንፈሳዊ ሕግ ውስጥ ለመኖር ካልፈቀደ ራሱን ያጠፋል።

1. መለያየት

ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ይለያየዋል። አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ ኃጢአት ስለ ሠሩ ከእግዚአብሔር ፊት ለመደበቅ ሞከሩ። እግዚአብሔር ለእነርሱ ካዘጋጀላቸው መልካም ከሆነው ከገነት ቤታቸው ውስጥ አስወጣቸው። መለያየት የሰው ምርጫ ነው። ኃጢአትን መሥራት እስካልተውን ድረስ እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ አድርጎ እንዳይቀበለን ፍጹም ባሕርዩው አይፈቅድልንም። በክርስቶስ እምነት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እስካልሆንን ድረስ ኃጢአት ወደ ሰማይ እንዳንገባ በሩን ይዘጋብናል። የእግዚአብሔር ፍርድ ኃጢአትን አጥፍቶ ኃጢአተኞችም እንዲቀጡ ይጠይቃል፤ የእግዚአብሔር ምሕረት ኃጢአታችን እንድንናዘዝና ወደ እርሱም እንድንመለስ ምቹ የሆነ ጊዜ ይሰጠናል።

የዓለምን ሁኔታ ተመልከቱ። በመፋታት ምክንያት ብዙ ቤተሰቦች ስለምን ይሠቃያሉ? ይህን ያህል ብጥብጥ፥ ሞገደኝነትና ወንጀል ሊፈጸም የቻለው ለምንድን ነው? ጽኑ ሰላም ለማቋቋም የሚደረገው ድካም ሁሉ ለምን ከንቱ ሆኖ ይቀራል? ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እየተዋጋ በጠርነት ላይ እስከተገኘ ድረስ ከራሱና ከሌሎች ጋር በሰላም ሊኖር አይችልም።

2. ስሕተት

ኃጢአት ሰዎች እውነትን እንዳያዩ ያሳውራል፤ እንዲሁም ማንኛውንም ዓይነት ስሕተት እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል። የዓለም ብርሃን ከሆነው ከክርስቶስ ሰዎችን ይለያል። ራሳቸው በፈጠሩት ጨለማ አስተሳሰብና የሐሰት ፍልስፍና ውስጥ ተሰናክለው

እንዲወድቁ ያደርጋቸዋል (ኤፌ. 4፡17-18፤ ማቴ. 15፡12-14፤ ዮሐ. 7፡17፥ 8፡12፤ ሮሜ 1፡18-32 አንብቡ)።

3. ኀዘን

ኃጢአት ከእግዚአብሔር ለይቶናል። ከእግዚአብሔር የሚመጣልንን በረከት፥ ሰላም፥ ደስታ፥ ፍቅርና ሕይወት እንዳናገኝ አግዶናል። ኃጢአት ብዙ ዓይነት ሥቃይና ኀዘን በዓለም ውስጥ አምጥቷል። በዚህ ዓለም ኑሮአችን ውስጥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ለመሥራትና መንገዱን እንድንከተል ለማስረዳት እየሞከረ ነው። በመልካምና በክፉ መካከል ሆነን በመዋጋት ላይ እንገኛለን። ደስታ ከኀዘን ጋር ተደባልቋል። ሰዎች በከፊል መልካም፥ በከፊል ክፉዎች ናቸው። እግዚአብሔርን ብንመርጥ እርሱ ፍጹም ወደሆነውና ወደማያልቀው ደስታ ይመራናል። እነዚያ ኃጢአትን የሚመርጡ ለጊዜው መልካም ደስታ ያገኙ ይሆናል፤ ነገር ግን ሁሉን እንዲያጡና ለዘላለም መልካም የሆነውን ሁሉ እንዳያገኙ ይደረጋሉ።

ኢየሱስ ላልዳኑት ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ሕይወት ሲናገር የአካልና የአእምሮ ጣርና ኀዘን እንደሚያገኛቸው ተናግሯል። (ማቴ. 24፡51፤ 25፡30 እና ሉቃስ 16፡19-31 ከራእይ 21፡1-4 እና ዕብ. 11፡24-26 ጋር አነጻጽሩ)።

4. ባርነት

ኃጢአት ኃጢአተኛውን ባሪያ አድርጎ የሚደርስበትን ፈተና እንዳይከላከል ኃይሉን ያሰርቅበታል። አንዳንድ ሰዎች ለሆዳቸውና ለልማዳቸው ባሪያዎች ይሆናሉ። ሊቆጣጠሩት በማይችሉት ቁጣ፥ ቅናትና በደል ተነድተው ወንጀል ውስጥ ይገባሉ። ለኃጢአት የበለጠ በፈቀድንለት መጠን ኃይሉ በላያችን ላይ ታላቅ ይሆናል። አንዳንዶች በአጋንንት ተጠምደው ሌሎችን ለመጉዳት በሰይጣናዊ ኃይል ይጠቀማሉ። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥልጣን የሚከዱትን ሁሉ እያታለለ ነፃ ለማውጣት ተስፋ ይገባላቸዋል፤ ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ መልሶ ባሪያዎች ያደርጋቸዋል (ዮሐ. 8፡34-36)።

5. ሞት

ኃጢአት እስረኞቹን ይዞ እኛ በአእምሮአችን አስበን ልንደርስበት ከማንችለው ባሻገር ወደሚገኘው ሞት ይወስዳቸዋል፤ ይኸውም ለዘላለማዊ ሥቃይና ኀዘን ከእግዚአብሔርና መልካም ከሆነው ነገር መለየት ማለት ነው። ሰይጣንና ርኩሳን መናፍስት ባሉበት ስፍራ ለዘላለም ይዘጋባቸዋል። (ማቴ. 25፡41፤ ራእይ 20፡11-15፤ 21፡8 አንብቡ።)

| የሰውነት ክፍሎች | የእግዚአብሔር ስጦታ | የሰው አጸፋ | የኃጢአት ውጤቶች |
|---|---|---|---|
| አእምሮ<br>ስሜቶች<br>ፈቃድ<br>ፍጹም ሰው | እውነት<br>ፍቅር<br>ሥልጣን<br>ፍጹም ክርስቶስ | ያለማመን<br>ግድ የለሽነት<br>መሸፈት<br>ፍጹም ክሕደት | ስሕተት<br>ኀዘን<br>ባርነት<br>ፍጹም ሞት |
| ኢሳ. 58፡1 እና መዝ. (139)፥17 አንብቡ። | | | |

## ጥያቄዎች

1. የኃጢአት በሽታ ራሱን የሚገልጸው እንዴት ነው?
2. በአንድ ሰው ወይም በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ኃጢአት የሚገለጽበት በሮሜ 1 ውስጥ የምንመለከተው የመጀመሪያው እርምጃ ምንድን ነው? ያዕ. 1፡15።
3. የኃጢአት የመጨረሻ ውጤት ምንድን ነው? ያዕ. 1፡15።
4. ኃጢአት እግዚአብሔርን መካድ ማለት ነው። እግዚአብሔርን የምንክድባቸው ሦስቱ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?
5. ኃጢአት ማለት በሕይወት ውስጥ የተሳሳተ ዓላማ ወይም ዕቅድ መያዝ ማለት ነው። እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለው ዓላማና ዕቅድ ምንድን ነው?
6. ታላቁ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ምንድን ነው? ለዚህ ትእዛዝ ሰው ሁሉ ታዛዥ ሆኗል?
7. ስለ ኃጢአት ለሌሎች በምንሰብክበት፥ በምናስተምርበትና በምንመሰክርበት ጊዜ የእኛ ሁኔታ ምን ዓይነት ሊሆን ይገባል?
8. ስለ ኃጢአት የተሰጠውን የክርስቶስን ማዳን ካልተቀበልን የሚደርሱብን የኃጢአት አደጋዎች ወይም ውጤቶች ምንድን ናቸው? አምስት መልሶችን ስጡ።

# ትምህርት 6

## የደኅንነት ምልክቶች

1. እግዚአብሔር አብ ዓለምን ይወዳል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ያድናል።

- ክርስቶስ ምትካችን
- ክርስቶስ አማላጃችን
- ክርስቶስ ነፃ አውጪአችን
- ክርስቶስ ጌታችን።

መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው ለውጥ

- የመንፈስ ቅዱስ ሥራ
- የሰው ኃላፊነት

### 1. እግዚአብሔር አብ ዓለምን ይወዳል

በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ያለን ድርሻ ስለ ኃጢአትና ስለሚያመጣው ውጤት መናገር ብቻ አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል ከኃጢአት ለመዳን መንገድ ይሰጠናል።

እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ ባይሆን ኖሮ በዓለም ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ ባጠፋቸው ነበር። ሰዎች እንዲድኑ እግዚአብሔር አያስገድድም። ከኃጢአታቸው እንዲመለሱና የእርሱን የማዳን መንገድ እንዲቀበሉ ግን ደግሞ ደጋግሞ መልእክተኞችን ይልካል። በማንኛውም ስፍራ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸውና ሊያድናቸው እንደሚፈልግ ልንነግራቸው ይገባል። (ሕዝ. 33:11፤ ዮሐ. 3:16፤ 1ኛ ጢሞ. 2:3-6፤ ሮሜ 2:4፤ 1ኛ ዮሐ. 4:9-10 አንብ)።

### 2. ኢየሱስ ክርስቶስ ያድናል

ከኃጢአትና ኃጢአትም ከሚያስከትለው ውጤት መፍትሔ የሚያስገኝልን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰው ልጆች ላይ ለሚደርሰው ችግር ሁሉ መፍትሔ የሚያስገኘው እርሱ ነው። የምንሰብከው የወንጌል ትምህርት ብቻ በቂ አይደለም። ሰዎች ራሳቸውን ከአዳኙ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሊያስተዋውቁ ይገባል (ዮሐ. 17:3 እና 1ኛ ቆሮ. 1:23-24)።

ሀ. ክርስቶስ ምትካችን (2ኛ ቆሮ. 5:21)

ዓላማ፡- ክርስቶስ የእኛ ምትክ በመሆኑ ሰዎች ኃጢአታቸው በምን አኳኋን ሊሰረይላቸው እንደሚችል ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን አንዳንድ ጥቅሶችን እያወጣችሁ ማስረዳት እንድትችሉ ለመርዳት ነው።

ክርስቶስ እኛን ለማዳን መሞቱ ያስፈለገበትን ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ገና አልተረዱም፤ አንዳንዶቹ ደግሞ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለተገለጸው ስለ እንስሳት መሥዋዕት ይጠይቃሉ። በብሉይ ኪዳን የእንስሳ መሥዋዕት ይደረግ የነበረው ኃጢአት ሊደመሰስ የሚችለው በኃጢአተኛው ሞት ወይም ለእርሱ ፍጹም ምትክ በሚሆን ነገር ብቻ መሆኑን ለሕዝቡ ለማሳወቅ ነበር። የእንስሳ መሥዋዕት ኢየሱስ ደሙን በማፍሰስና ሕይወቱን በመስጠት ሰውን እንዴት እንደሚያድን የሚያስረዳ ሥዕላዊ ምሳሌ ነበር። እግዚአብሔር ስለ ኃጢአት የእኛ ምትክ እንዲሆን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለላከ ዛሬ የእንስሳ መሥዋዕት አያስፈልገንም። ኃጢአታችን ያስከተለብንን ቅጣት እርሱ ስለተቀበለልን በነጻ ልንሄድ እንችላለን። ሆኖም ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ ምትክ መሆኑን አምነን መቀበል ይኖርብናል። (ዕብ. 10፡3-4፤ 9-10፤ ዮሐ. 1፡29፤ 3፡16፤ ዕብ. 9፡28 አንብቡ።)

ክርስቶስ ኃጢአታችን ያስከተለብንን ቅጣት ተቀብሎ በእኛ ምትክ ሞተ፤ የእርሱም ጽድቅ ለእኛ ተቆጥሮልናል። ስለ ኃጢአት ወይም የእግዚአብሔርን ሕግ ስለ ማፍረስ የሚሰጠው የመጨረሻ ቅጣት ሞት ነው። ሰውን ከዚያ ቅጣት ለማዳን ኃጢአት ያልሠራ ሌላ ሰው የእርሱ ምትክ እንዲሆን ያስፈልግ ነበር፤ ኃጢአትን ያልሠራ የእግዚአብሔርና የሰው ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ኃጢአታችን በእርሱ ላይ ፍርድንና ሞትን አስከተለበት፤ እርሱን እንደ አዳኛችን አድርገን ስንቀበል ኃጢአታችን ሁሉ ይሰረይልናል። ኃጢአታችን በመስቀሉ ላይ ተፈርዶበታል። (ኢሳ. 53፡5-6፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21፤ ሮሜ 5፡6፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡3 አንብቡ።)

ለ. ክርስቶስ አማላጃችን (ዕብ. 7፡25-26)

ዓላማ፡- ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ አማካይነት እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት መፍጠር እንደሚችሉ አንዳንድ ጥቅሶችን በመጠቀም ማስረዳት እንድትችሉ ለማስተማር ነው።

ዛሬ በዓለም ውስጥ ተፈላጊ የሆነው ነገር አማላጅ ማግኘት ነው። አረኞችና አማካሪዎች ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው እንዲግባቡ በማድረግ ብዙ ጋብቻዎችንና ቤቶችን አድነዋል።

በመንግሥታትም መካከል አማላጅ ማግኘት አስፈላጊ ሆኗል፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከልም እንደዚሁ አማላጅ ያስፈልጋል። እግዚአብሔርንና ሰውን አንድ ማድረግ የሚችል ክርስቶስ ብቻ ነው።

ኢየሱስ በእኛ ምትክ በመሞቱ እግዚአብሔር የሚጠይቀውን ፈጽሟል። ከእንግዲህ ወዲህ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆች እንጂ ጠላቶች አይደለንም።

የሰው ድርሻ ክርስቶስን እንደ አዳኝ አድርጎ መቀበልና ኃጢአቱን ተናዝዞ ይቅርታ ማግኘት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን የምንፈጥረው በክርስቶስ ነው። አዳኛችንና ጌታችን አድርገን ሕይወታችንን ለክርስቶስ ስንሰጥ ይህ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን የሰላም ስምምነታችን ነው። እግዚአብሔር ሰላም ለመፍጠር የሚጠይቀውን ሁሉ ክርስቶስ ፈጽሞታል፤ እኛንም ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ለማድረግ ለሚፈልጉ ሁሉ እንድናውጅ ልኮናል። (1ኛ ጢሞ. 2፡3፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡20፤ የሐዋ. 10፡34-43 አንብቡ።)


ሐ. ክርስቶስ ነፃ አውጪአችን፡ (ዮሐ. 8፡31-36፤ 2ኛ ቆሮ. 3፡17)


ዓላማ፡- አንዳንድ ጥቅሶችን በመጠቀም ክርስቶስ ከኃጢአት ኃይል ነፃ በማውጣት ስለሚሰጠው ነጻነት ማስረዳት እንድትችሉ ለማስተማር ነው።


ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአትና ከሰይጣን ኃይል አርነት የሚሰጥ ታላቅ ነፃ አውጪ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ከጥላቻ፥ ከጠብ፥ ከሆዳምነት፥ ከፍትወት፥ ከትዕቢትና ከራስ ወዳድነት ነፃ ያወጣል። እርሱን የሚቀበሉትን ሁሉ ከሞት አውጥቶ በሁሉም አቅጣጫ ጤንነት ይሰጣል።

ዛሬ ዶክተሮች ልብን በቀዶ ጥገና መቀየር ችለዋል። በአንድ አደጋ ከሞተ ጤናማ ሰው ሰውነት ውስጥ ልብን አውጥተው የታመመውን በሽተኛ ሰው ልብ ቆርጠው በማውጣት ጤናማውን ልብ ለመተካት ችለዋል። በመንፈሳዊ መንገድ ክርስቶስ ለእኛ የሚያደርግልን ነገር ይህንን ይመስላል። መዝ. 50(51)፡10 አንብቡ። የሆነ ሆኖ ማዳን ማለት የልብ ቀዶ ጥገና ማድረግ ማለት ሳይሆን በቅዱስ መንፈሱ አማካይነት ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ሲያድር ማለት ነው። ከወንጀል፥ ከሽፍትነት፥ ከፍርሃትና ከኃጢአት ሁሉ እርሱ ነፃ ያወጣናል። (ዮሐ. 8፡31-36፤ ሮሜ 6፡6 አንብቡ።)

ለመዳን አንድ ኃጢአተኛ በንስሐ መመለስና ማመን ይኖርበታል። በንስሐ መመለስ ማለት ስለ ኃጢአት ፍጹም የተለወጠ አስተሳሰብ መያዝ ማለት ነው።




በንስሐ መመለስ ማለት ስሕተት መሥራታችንን አምነን በአእምሮአችን ውስጥ ስለ ኃጢአት ያለንን ሁኔታ መለወጥ ማለት ነው። ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛችን በውስጥ ስሜታችን ማዘንና ጥፋተኛነታችንም የሚያስከትልብንን ቅጣት መፍራት ማለት ነው። በፈቃዳችን ውስጥ ከኃጢአት ለመመለስ ውሳኔ እናደርጋለን (ሕዝ. 33:11 አንብቡ)። በንስሐ እንድንመለስ የሚመራን መንፈስ ቅዱስ ነው። በአእምሮአችንና በስሜታችን ውስጥ ሆኖ ኃጢአት መሥራታችንን ያስረዳናል፤ እንዲሁም መንገዳችንን መለወጥ የሚያስፈልገን መሆኑን ያሳየናል፤ ከኃጢአት ወደ እግዚአብሔር እንድንመለስ ፈቃዳችንን ያጠነክረዋል።

ወደ ንስሐ የሚመራን መንፈስ ቅዱስ ከሰዎች ጋር በልዩ ልዩ መንገዶች ይሠራል። አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ሲሠራ

ያለቅሳሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ በስሜት ተገፋፍተው ክርስቶስን ለመከተል ውሳኔ ያደርጋሉ፤ ሌሎች ደግሞ ፈጣንና ግልጽ የሆነ ውሳኔ ይሰጣሉ። አንዳንዶች ግን ኃጢአተኞችና ንስሐ የሚያስፈልጋቸው መሆናቸውን እስኪረዱ ድረስ ጊዜ ይወስድባቸዋል፤ ከዚያ በኋላ ያምናሉ።

መ. ክርስቶስ ጌታችን (ሮሜ 10፡9፤ ዮሐ. 14፡15)

ዓላማ፡- በክርስቶስ የሚገኘው ሕይወት ችግራችንን፥ የመኖራችንን ዓላማና የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንዴት እንደሚሞላው እርእስቶቹን በመጠቀም ማስረዳት እንድትችሉ ለማድረግ ነው።

ክርስቶስ ወደ ሰማይ የሚወስደው መንገድ መሆኑን ማወቅ ብቻ አይበቃም፤ ወደሚመራን መከተል አለብን። እርሱን እንደ አዳኛችን መቀበል ብቻ ሳይሆን የሕይወታችንም ጌታ መሆኑን መረዳት አለብን። እርሱ እውነት ነው። እርሱ የሰጠው ትምህርት የተስፋችን፥ የማንነታችንና የዕለት ተዕለት ሕይወታችን መሠረት ነው። በሕይወታችን ውስጥ ያለን ዓላማ እግዚአብሔርን ማክበርና ለእርሱ እስከ ዘለዓለም መታዘዝ ነው። እርሱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለእያንዳንዳችን ልዩ የሆነ ቦታና ከእኛም የሚጠብቀው ልዩ የሥራ ድርሻ አለ። (ዮሐ. 10፡1-6 አንብቡ)።

## 3. መንፈስ ቅዱስ የሚያስገኘው ለውጥ

ዓላማ፡- መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ስለፈጠረው ለውጥና ሰዎች ለመዳን መለወጥ እንዳለባቸው የሚገልጹ ጥቅሶችን በመጥቀስ ማስረዳት እንድትችሉ ለማስተማር ነው።

ሀ. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ (2ኛ ቆሮ. 5፡17፤ ዮሐ. 14፡26፤ 16፡7-11)

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና እንደ ጌታችን ስንቀበለው መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ መጥቶ ያድራል። እርሱ አቅጣጫችንን ለውጠን በሰማዩ መንገድ ውስጥ ጉዞአችንን እንድንጀምር አድርጎናል።

በአሳባችን በእግዚአብሔር ላይ ስንሸፍት የያዝነውን ጥላቻ፥ ክፉ አሳብና ፈቃድ ለውጠን በንስሐ እንድንመለስ ረድቶናል። በክርስቶስ እንድናምን እምነትን ሰጥቶናል።


አዲስ ፍጥረትም እንድንሆን አድርጎአል (2ኛ ቆሮ. 5፡17-18፤ ዮሐ. 3፡3-6)።


ክርስቶስ በመንፈሱ በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ መንፈስ ቅዱስ እኛን ከክርስቶስ ጋር አገናኝቶ የእርሱ የአካሉ ብልት አድርጎናል፤ አካሉም

ቤተ ክርስቲያን ናት። በክርስቶስ ባገኘነው አዲስ ልደት የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። መንፈስ ቅዱስ መልካም አሳብ እንዲኖረንና ትክክለኛ ስሜት እንድናገኝ ይረዳናል (ፊልጵ. 2፡13)። ትክክለኛ አሳብና ትክክለኛ ስሜት ወደ ትክክለኛ ሥራ ይመራናል። (ሮሜ 8፡1–17 አንብቡ።)

### ለ. የሰው ኃላፊነት (1ኛ ዮሐ. 1፡9፤ ዮሐ. 1፡12፤ የሐዋ. 2፡38)

እግዚአብሔር ማንንም ቢሆን አያስገድድም። ሰዎች እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን አዲስ ሕይወት ለማግኘት እጅግ ይፈልጉ ይሆናል፤ ነገር ግን ለማግኘት ፈቃደኞች ካልሆኑ ሊሰጣቸው አይችልም።




ንስሐ ከወንጌል መልእክት መካከል አንዱ ነው። ማንንም ለማስቀየም ስለማንሻ ይህን ክፍል ለማስተማር አንፈልግ ይሆናል።

ሰዎች እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ለማሳየት ስንፈልግ አንዳንድ ሰዎች መብት የላችሁም ይሉን ይሆናል። አንድ ሐኪም ሕመምተኛውን ይጎዳል ብሎ መርፌ ከመውጋት ይቆጠባል? አንድ የእሳት አደጋ ሠራተኛ ሰዎችን ከሚቃጠለው ቤት ለማውጣት በር ከመስበር ወደ ኋላ ይላል? ወደ ፍርድ የምንቀርብበት ጊዜ እንደ ደረሰ እንድናውቅ እግዚአብሔር ይርዳን። ጊዜውም ከማለፉ በፊት ሰዎችን በንስሐ እንዲመለሱ ለማድረግ እንጣደፍ (2ኛ ጢሞ. 4፡1–2፤ የሐዋ. 2፡38፤ 16፡30–31።)

አዳዲስ አማኞች ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንዲቀጥሉ እናበረታታቸው። (2ኛ ቆሮ. 3፡18 አንብቡ።) ሰዎች ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመለከቱ የተቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን። (2ኛ ጢሞ. 2፡9–10 አንብቡ።)

ማስታወሻ፡– ንድፉ ቀላል ስለሆነ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ወይም ከፍ ባለ ወረቀት ላይ ለመሣል ሞክሩ። ሥዕልን በማየት ሰዎች በቀላሉ ነገሮችን ማስታወስ ይችላሉ።

## ጥያቄዎች

1. ደኅንነትን በሚመለከት፡–

   ሀ. ስለ እግዚአብሔር የምናስተምረው ምንድን ነው?

   ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ ለማዳን ሲል ያዘጋጃቸው አራት ነገሮች ምንድን ናቸው?

2. በደኅንነታችን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንድን ነው?

3. ለደኅንነታችን ያለብን ኃላፊነት ምንድን ነው?

# ትምህርት 7

# ሰዎች ክርስቶስን እንዲቀበሉ መርዳት

መሰናክሎችን ማስወገድ

- የማያዛልቅ ተስፋ
- የክርስቲያኖች ኃጢአት
- ከንቱ ትርፍ
- ቀጠሮ ማብዛት
- ማመንታት

ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለሰዎች ማሳየት

- በኢየሱስ ማመን
- ኃጢአትን መናዘዝ
- ይቅርታ መጠየቅ
- መቀበልና ማወቅ
- ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል

ከማያምኑ ሰዎች ጋር መጸለይ

- የኅብረት ጸሎት
- የግል ጸሎት

## 1. መሰናክሎችን ማስወገድ

ይህ ጥናት ለልዩ ልዩ ሰዎች የመዳንን መልእክት እንድናስረዳቸው ይረዳናል።

አንድ ሰው ክርስቶስን አምኖ ለመቀበል የሚያግደው ነገር ምን እንደሆነ ለይተን ካወቅን እርሱን ለመርዳት ቀላል ይሆንልናል።

መዳን ለሚፈልጉ ሰዎች ሰይጣን በአእምሮአቸው ውስጥ የሚዘራቸው አምስት ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ እንመርምር።

ሀ. የማያዛልቅ ተስፋ

ዓላማ፡- መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀም ሰዎች የሚያምኑበት ነገር ምን እንደሆነ ለመንገርና በማያዛልቅ ተስፋ ላይ እንዳይመረኮዙ በማስረዳት ክርስቶስን እንዲያምኑ ለማስተማር እንድትችሉ ለማሳየት ነው።

ብዙ ሰዎች በክርስቶስ ሳይሆን በሌሎች በተሳሳቱ ነገሮች ለመተማመን ሲሞክሩ ይታያሉ። ለሰዎች ትክክለኛ መስለው የሚታዩ ነገሮች አሉ፤ ነገር ግን ትክክል አይደሉም። (ምሳሌ 4፡12፤ ማቴ. 7፡24-29 አንብቡ።)

«መንገዶች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የሚመሩ ናቸው። አንተ ትክክለኛ ከሆንህ ሃይማኖትህም እንደሌላው መልካም ነው» ተብሎ ሲነገር አልሰማችሁም? (1ኛ ጢሞ. 2፡15፤ ዮሐ. 14፡6 አንብቡ።)

በዘመናችን ሰዎች ከፈጣሪአቸው ጋር ሰላም ለመፍጠር በብዙ የተለያዩ ነገሮች ላይ ሲደገፉ ይታያሉ። ዝቅ ብለው ከተዘረዘሩት ነገሮች

መካከል የክርስቶስን ጥሪ የሚቃረኑ ወይም የእርሱን የማዳን ሥራ ለመሻማት የሚቃጡ የትኞቹ ናቸው?

| | |
|---|---|
| ሌሎች ሃይማኖቶች | የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን |
| መናፍስት | የወላጆች ሃይማኖቶች |
| መላእክት | ቅዱሳን |
| አባቶች | ድሆች ሰዎችን መርዳት |
| መልካም ኑሮ | ለቤተ ክርስቲያን ስጦታዎችን መስጠት |
| ገንዘብ | መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ጣዖት ማምለክ |
| ራስን ማጎሳቆል | ጥንቆላ ወይም አስማት |
| የራስ ጥረት | |
| የቤተ ክርስቲያን ወግና | |
| ሥርዓትን መፈጸም | |

ብዙዎች በክርስቶስ በማመን ፈንታ በቤተ ክርስቲያን አባልነት ያምናሉ። ብዙዎች እምነትን በክርስቶስ ላይ በማድረግ ፈንታ በራሳቸው ይተማመናሉ። ራሳቸው መልካም እንደሆኑና አዳኝም እንደማያስፈልጋቸው ይሰማቸዋል። ሌሎች ደግሞ በራሳቸው ጥረት ላይ ይመካሉ። ሰይጣን ብዙ ሰዎች በራሳቸውና በጥረታቸው እንዲተማመኑ ያደርጋቸዋል።

ብዙዎች ኢየሱስን እንደ ምሳሌያቸውና እንደ አስተማሪያቸው ሲያደርጉት፥ እንደ ግል አደኛቸው ግን አድርገው አይቀበሉትም። ዮሐንስ 3፡3-7 እነዚህ ሰዎች የግል ጥረታቸው ከኃጢአት እንደማያድናቸው እንዲገነዘቡ ሊረዳቸው ስለሚችል በጥንቃቄ አጥኑት።

ለ. የክርስቲያኖች ኃጢአት

ዓላማ፡- በክርስቲያኖች ኃጢአት ምክንያት የተሰናከሉትን ሰዎች ለመርዳት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀረቡት ምሳሌዎች ለመጠቀም እንድትችሉ ለማስረዳት ነው።

ክርስቲያኖች ፍጹም አይደሉም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ሰው ውድቀት ላይ ይሠራል። እግዚአብሔር በሌሎች ላይ ስለ መፍረድ ለእርሱ እንድንተው በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ይነግረናል (ማቴ. 7፡1-3፤ ሮሜ 2፡1-3።)

ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ብዙዎች ሰዎች እውነተኛ ክርስቲያኖች አይደሉም። ክርስቲያን ነን በሚሉ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን በእውነት በማያምኑና እንደ አዳኛቸው አድርገው ባልተቀበሉት ላይ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።

ሐሰተኛ ገንዘብ በገበያ ላይ ውሏል ብለን ገንዘብን ሁሉ አንቀበልም እንላለን? አንዳንዶች እውነተኞች አማኞች አይደሉም ብለን ለምን በሚሊዮን የሚቆጠሩ እውነተኛ አማኞች የተቀበሉትን ክርስትና አንቀበልም እንላለን?

ክርስቶስን ያልተቀበለ ሁሉ ክርስቲያን ስላልሆነ ክርስቲያን ተብሎ በሚጠራ ሕዝብ ስሕተት ላይ ልንፈርድ አንችልም፤ ምክንያቱም ፍጹም ክርስቲያን ነው ተብሎ የሚጠራ ሕዝብ የለም።

ሐ. ከንቱ ትርፍ

ዓላማ፡- በከንቱ ትርፍ ፍለጋ ሳትቅበዘበዙ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጡትን ዘለቄታዊ ትርፎች ለማግኘት እንድትችሉ ለማስረዳት ነው።

በዚህ ዓለም ሰማንያ ዓመት በምቾት ከሚያስቀምጥ ቤትና ከእርሱ በጣም የተሻለ በሰማይ ለዘላለም ከሚያኖር ቤት የትኛው ይሻላል? ጊዜያዊ መከራ ወይም የዘላለም ደስታ? በምድር ላይ ሀብታም መሆን ወይም በሰማይ? በሰው ተቀባይነት ማግኘት ወይስ በእግዚአብሔር? ዓለም የሚሰጠውን ማግኘት ወይስ እግዚአብሔር የሚሰጠውን? ለእነዚህ ጥያቄዎች ብዙ ሰዎች የተሳሳተውን መልስ ይመርጣሉ። በተሳሳተው የኑሮ አቅጣጫም ይኖራሉ፤ ሉቃስ 15፡11-24፤ ዮሐ. 10፡10፤ ዕብ. 11፡24-26።

በእግዚአብሔር ቃል የተለካ ትርፍ ብቻ ጽኑ ዋጋ ያለው ይሆናል። (ማር. 8፡36፤ ዮሐ. 12፡43፤ ሮሜ 8፡18 አንብቡ።)

መ. ቀጠሮ ማብዛት

ዓላማ፡- ክርስቶስን ከመቀበል መዘግየት አደገኛ እንደሆነና ዛሬውኑ መቀበል ጠቃሚ መሆኑን መረዳት እንድትችሉ ለማስተማር ነው።

ቀጠሮ ማብዛት አንዱ የሰይጣን ዘዴ ነው። ሰዎች የመጨረሻው ጊዜ እስኪደርስ ድረስ እንዲዘገዩ ያደርጋል። «አሁን ተደሰቱ፤ ክርስቶስን በኋላ ትቀበላላችሁ። አሁን ብዙ ሥራ አለባችሁ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሌላ ጊዜ ትሄዳላችሁ። ወጣት የምትሆኑት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ እስከታረጁ ድረስ ጠብቁ» እያለ ሰይጣን ይመክራችኋል። (ያዕ. 4፡13-14፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡2 አንብቡ።)

አንድ ወዳጃችሁ ስጦታ ይዞላችሁ ቢመጣ ስጦታህን እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን ዛሬ አልቀበልህም ትሉታላችሁ? ወደ ቤታችሁ ውስጥ እንዲገባ ሳትጋብዙት በሌላ ቀን ተመለስ ትሉታላችሁ? ብዙዎች ይህንን በልባቸው በር ቆሞ የሚያንኳኳውን የሰማዩን ጌታ እንደዚህ ይሉታል፤ (ራእይ 3:20፤ ኢሳ. 55:6፤ ምሳሌ 27:1፤ 2ኛ ቆሮ. 6:2።)

ሠ. ማመንታት

ዓላማ፡— ክርስቶስን ለመቀበል የሚያመነቱ ሰዎች ያለባቸውን ችግር በቅንነት አውቀን፥ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት እንድንረዳቸው ለማስተማር ነው።

ኢየሱስ «አትፍሩ!» ብሎ እንደተናገረ አስታውሱ። (ኢሳ. 43:13 አንብቡ።) ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነገሮች ሰዎች ክርስቶስን እንዳይቀበሉ ከሚከለክሏቸው ውስጥ አንዳንዶቹ ናቸው።

1. የቤተ ክርስቲያናችንን ወግና ሥርዓት ባንፈጽም ወይም መናፍስትን ባናመልክ እንዲሁም ለሰይጣን መሥዋዕት ባናቀርብ ምን ይደርስብን ይሆን? ብለው ያስባሉ (1ኛ ዮሐ. 4:4።)

2. መከራን መፍራት

አንዳንዶች የቤተሰቦቻቸውን ወይም የወዳጆቻቸውንና የማኅበራቸውን ተቃውሞ ይፈራሉ። አንዳንዶች ደግሞ መሳቂያ እንዳይሆኑ ሲፈሩ ሌሎች ደግሞ ስደትንና ሥቃይን ይፈራሉ። እነዚህን ሁሉ በጸሎት ልንረዳቸው እንችላለን። ምንም ነገር ቢደርስባቸውም እንኳ እግዚአብሔር ሊያጠነክራቸው እንደሚችል ልናሳያቸው እንችላለን። ለእኛ ስለሞተው ስለ እንዱ መከራን ብንቀበል ክብር እንደሆነ ልንገልጽላቸው እንችላለን። ለእርሱ የሚሠቃዩትን ሁሉ ዋጋቸውን እንደሚከፍላቸው ልንነግራቸው ይገባል፤ (ማር. 8:34–38፤ ሉቃ. 6:22–23፤ 2ኛ ጢሞ. 2:12፤ ዕብ. 12:2–3።)

3. ውድቀትን መፍራት

ወንጌል እውነት እንደሆነ አውቃለሁ፤ ነገር ግን በክርስትና ሕይወት ለመኖር አልችልም የሚል ሰው አጋጥሟችሁ ያውቃል? ሌሎች ደግሞ በቤተሰቤ፥ በማኅበሬ ወይም በሥራዬ ውስጥ ያለውን ችግር ልታውቁት አትችሉም ይላሉ። እንወድቃለን ብለው መልካም ክርስቲያን ለመሆን ስለሚፈሩ ሰዎች ምን እንላለን? (2ኛ ቆሮ. 2:9፤ 1ኛ ቆሮ. 10:13 አንብቡላቸው።)

የተቀሩትን ሰዎች ደግሞ የምንረዳቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ እነርሱ የምንጸልይ መሆኑን በመንገር ነው። ቢደናቀፉም ደግሞ በ 1ኛ ዮሐ. 1:9 በተገለጸው መሠረት እንደገና ይቅርታ አግኝተው

ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትን እንደሚፈጥሩ አናረጋግጥላቸው (ሮሜ 8፡31–39 አንብቡ።)

አንድ አዲስ አማኝ እንደ አንድ ሕፃን ይቆጠራል። መረዳትና መበረታታትን ይፈልጋል። ከክርስቶስ ተለይተው የወደቁትን ሰዎች መልሶ ለማምጣት ምን ማድረግ ይገባናል?

4. በእግዚአብሔር ከመጣል መፍራት

አንዳንድ ሰዎች ከወደቁ በኋላ ይቅርታ ማግኘት የማይችሉ ይመስላቸዋል። የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘት ገና ምኞት ካላቸው መንፈስ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔርን ሊስባቸውና ይቅርታ ሊሰጣቸው እንደሚችል ያረጋግጥላቸዋል። እግዚአብሔርን እንደ ጠላቸው አድርገው በመፍራት ለሚያስቡ ሰዎች እነዚህን ጥቅሶች አንብቡላቸው፤ ዮሐ. 3፡16፤ 6፡37፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡7 እና 9። በኃጢአታቸው እንዲናዘዙና እግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚያደርግላቸው አሳስቧቸው።

2. ሰዎች ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ማስረዳት

ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን ከሰሙና ኃጢአታቸውን ከተረዱ በኋላ ለመዳን ምን መሥራት እንደሚገባቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል? መዳን ስጦታ ነው፤ ነገር ግን ይህንን ለመቀበል ምን ማድረግ ይገባቸዋል?

ሀ. በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን (የሐዋ. 16፡31፤ ዮሐ. 3፡16)

ለ. ኃጢአትን መናዘዝ

ሰዎች መቀጣት ስለማይፈልጉ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲላቸው ይለምናሉ፤ ነገር ግን ኃጢአትን ከመሥራት ለመቆጠብ አያቅዱም። አንዳንዶቹ ደግሞ ለይስሙላ ኃጢአታቸውን ቢናዘዙም እንኳ ከልባቸው ውስጥ ሽፍትነትን አያስወግዱም (የሐዋ. 3፡19፤ ማር. 1፡15።)

ሐ. ይቅርታ መጠየቅ

ኃጢአትን መናዘዝና ይቅርታን መጠየቅ በአንድ ጊዜ ሊፈጸሙ የሚችሉ ነገሮች ናቸው። (1ኛ ዮሐ. 1፡9 አንብቡ)። ሆኖም አንዳንዶቹ ኃጢአታቸውን ሲረዱና በነገሩም ሲያዝኑ ለእግዚአብሔር ተናዝዘው ይቅርታን አይጠይቁም። ለይቅርታ ወደ እርሱ መቅረብ ይኖርብናል [መዝ. (51)፤ ሉቃ. 18፡13፤ ማቴ. 6፡9–12 አንብቡ]።

መንፈስ ቅዱስ አንዳንዶቹን የተለያዩ ኃጢአቶችን እንዲናዘዙ ሊመራቸው፥ ሌሎችን ደግሞ ኃጢአታቸውን እንደ አንድ አድርገው

እንዲናዘዙ ያደርጋቸዋል። የእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ምን እንደሚያስፈልገው መንፈስ ቅዱስ ያውቃል።

መ. መቀበልና ማወቅ

ኢየሱስ ዓለምን ለማዳን እንደ ሞተ ማመን ብቻ በቂ አይደለም፤ እርሱን እንደ ግል አዳኛችንና እንደ ጌታችን ልንቀበለው ይገባል። (ዮሐ. 1፡12 አንብቡ።) ኢየሱስን ስንቀበለው እርሱ አዳኛችንና ጌታችን መሆኑን ለሌሎች ማሳወቃችን ነው (ሮሜ 10፡9–10።)

ሠ. ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል

በእውነት በክርስቶስ ስናምን ኃጢአታችንን ስንናዘዝና ይቅርታም ስንጠይቅ እርሱን ለመከተልና የእርሱን ትእዛዝ ለመታዘዝ ፈቃደኞች መሆን ይገባናል። እርሱ የሕይወታችን ጌታ እንዲሆን እንፈቅዳለን። (ሉቃስ 9፡23 አንብቡ።)

## 3. ከማያምኑ ሰዎች ጋር መጸለይ

ሀ. የቡድን ጸሎት

በአንዳንድ አገልግሎቶች ውስጥ ብዙ ሰዎች ጌታን ለመቀበል እንፈልጋለን ሲሉ እረኛው እነርሱን ወደ ጸሎት ስፍራ ይዟቸው በመሄድ እርሱን እየተከተሉ ከዚህ በታች የቀረበውን ጸሎት አብረውት እንዲጸልዩ ይጠይቅ፤ «ጌታ ሆይ፥ አንተን በድያለሁ፤ ነገር ግን ልጅህ ኢየሱስ የእኔን ኃጢአት ለመክፈል ሲል እንደሞተ አሳውቀኸኛል፤ ስለዚህ ይቅርታ እንድታደርግልኛና ኃጢአቴንና አለመታዘዜን እንድታስወግድልኝ እለምናለሁ። ኢየሱስ ሆይ፤ አንተን እንደ አዳኜና እንደ ጌታዬ አድርጌ እቀበልሃለሁ፤ በእኔ ምትክ ስለ ሞትክ አመሰግንሃለሁ፤ ይቅርታ እንዳደረክልኝ በማመን በአንተ አጋዥነት እከተልሃለሁ።»

እግዚአብሔር ልባቸውን ስለሚያውቅ ሰዎች በእውነተኛ የኅብረት ጸሎት መዳን ይችላሉ።

ለ. ከአዲስ አማኝ ጋር የሚደረግ ጸሎት

ከአዲስ አማኞች ጋር ስንጸልይ በራሳቸው ቃላት እንዲጸልዩ እናበረታታቸው፤ ሆኖም አንዳንዶች ዓይን አፋር ሊሆኑ ስለሚችሉ እንድንመራቸውና እኛን እየተከተሉ የምንናገራቸውን ቃላትም እንዲደግሙ ማድረግ ያስፈልገናል። የራሳቸውን እምነት የሚገልጡበት ንግግር በጣም ተፈላጊ ነው። (ሮሜ 10፡9–10 አንብቡ።)

ከሰዎች ጋር በምትጸልዩበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራችሁ ጠይቁ።

## ጥያቄዎች

1. በማናቸውም ሃይማኖቶች ማመን የእግዚአብሔር መንገድ አለመሆኑን በግልጽ የሚያስረዳ ጥቅስ ጥቀሱ።
2. ሰው በራሱ ጥረት መዳን እንደማይችል የሚገልጸውን ጥቅስ ጥቀሱ።
3. ክርስቲያኖች የሚፈጽሙትን ኃጢአት በመጥቀስ የክርስቶስን የማዳን ስጦታ ላለመቀበል ምክንያት ስለሚፈጥሩ ሰዎች የሚያስረዳው ጥቅስ የትኛው እንደሆነ ግለጹ።
4. ሰዎች ክርስቶስን ላለመቀበል የሚያውኳቸው ከንቱ ትርፎች የትኞቹ እንደሆኑ አስረዱ።
5. ይህንን ነገር በኋላ እናስብበታለን በማለት ቸል ለሚሉ ሰዎች ምን ማስጠንቀቂያ ትሰጡአቸዋላችሁ?
6. አንዳንድ ሰዎች መከራ እንዳይደርስባቸውና መዘባበቻ እንዳይሆኑ ይፈራሉ፤ እነርሱን ሊረዱዋቸው የሚችሉ ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?
7. ራሳቸውን በጣም ኃጢአተኞች አድርገው ለሚቆጥሩ ሰዎች የተሰጣቸው ተስፋ ምንድን ነው?
8. ከዚህ በታች ለተጠቀሱት ማመሳከሪያ ጥቅሶች ጥቀሱ።
   ሀ. በክርስቶስ ማመን
   ለ. ኃጢአትን መናዘዝ
   ሐ. ይቅርታን ማግኘት
   መ. ክርስቶስን መቀበልና መመስከር
   ሠ. ኢየሱስን መከተል።

# ትምህርት 8

# መመስከርና መምከር

የክርስቶስ ምስክር መሆን

- ምስክር የመሆን አስፈላጊነት
- የአንዱ ለሌላው መመስከር
- የምስክርነት ቡድኖች

በሥነ ጽሑፍ አማካይነት መመስከር

- ምክር በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ያለው ድርሻ
- ስለ ምክር የተሰጡ መሠረታዊ ደንቦች

- ለመምከር ምቹ የሆኑ ጊዜያት።

## 1. የክርስቶስ ምስክር መሆን

በኢሳ. 43፡10 ላይ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ «ምስክሮቼ ናችሁ» ብሏቸዋል። በሐዋ. ሥራ 1፡8 ኢየሱስ ለተከታዮቹ «ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» በማለት ይህንኑ ቃል ተናግሯል። ምስክር ማለት ምን ማለት ነው? ለክርስቶስ ምስክር ከመሆናችን በፊት ስለ እርሱ በግል የምናውቀው ነገር ሊኖረን ይገባል፤ በተጨማሪ ሕይወታችን የተለወጠ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል። እንዲሁም ስለ ኢየሱስ የምናውቀውን መናገር ይኖርብናል።

### ሀ. ምስክር የመሆን አስፈላጊነት

1. ስለ ክርስቶስ መመስከር እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች የወጠነው ዕቅድ ነው። ማንኛውም ሰው ሊሰብክና ሊያስተምር አይችልም፤ ግን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያውቅ ሁሉ ሕፃንም እንኳ ቢሆን ስለ እርሱ ለሌሎች ሊናገር ይችላል።

ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚያውቁት ሁሉ የእርሱ ምስክሮች እንዲሆኑ ኃይል ለመስጠት መንፈስ ቅዱስ መጥቷል። የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተው ስለ ኢየሱስ የሚያውቁትን ሁሉ መናገር ጀመሩ። ሐዋርያት ስለ እርሱ እንዳይናገሩ በሞት ቅጣት ቢያስፈራሩቸው እንኳ መመስከራቸውን አላቋረጡም።

2. ምስክርነት የወንጌል ማስፋፋት ሥራ መሠረት ነው። ሰዎች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ከመስጠታቸው በፊት የወንጌልን እውነት አስቀድመው ማየት ይፈልጋሉ (1ኛ ዮሐ. 1፡3)። የምንናገረው ነገር በሕይወታችን ውስጥ በግልጽ መታየት አለበት። ስለ ኢየሱስ የምታውቁትን ብቻ ተናገሩ እንጂ ምስክሮች ስለሆናችሁ ለክርክሮች ሁሉ መልስ መስጠት አያስፈልጋችሁም። (ዮሐ. 9፡25 አንብቡ።)

### ለ. የአንዱ ለሌላው መመስከር

ምስክርነታችሁ በዕቅድ ወይም ያለ ዕቅድ ሊሆን ይችላል። ሳይታሰብ ምቹ ጊዜያት ሊያጋጥሟችሁ ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ ምስክርነት የሚጀምረው ከቤተሰብና ከወዳጆች ነው፤ ይኸውም ኢየሱስ ሕይወታችሁን እንዴት እንደለወጠው ስለሚመለከት ነው። ክርስቲያናዊ ግብዣም ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ ሊረዳቸው ይችላል። ይኸውም ምናልባት በቤታችሁ ውስጥ ሰዎችን የእራት ወይም የሻይ ግብዣ በመጋበዝ ሊሆን ይችላል። እርስ በርሳችን አንድ በመሆንና የእግዚአብሔርን ቃል በመካፈል ልንጠነክር እንችላለን።

ጎረቤቶች በታመሙ፥ ባዘኑ ወይም በተቸገሩ ጊዜ እነርሱን በመርዳት መመስከር እንችላለን።

ሐ. በቡድን መመስከር

በስብሰባ ወቅት ክርስቶስ በሕይወታችን እንዴት እንደሠራ መመስከር ያልዳኑትን ሰዎች ወደ እምነት ለመመለስ በጣም ይረዳል። ከዚህ በፊት ከተጠቀምንባቸው የእግዚአብሔር ቃላት በማካፈል መመስከር እ [illegible] ሌሎች ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ይረዳቸዋል።

በቤታችን ውስጥ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ከሌሎችም ጋር የጸሎት ጊዜ በማድረግ ለሰዎች ልንመሰክር እንችላለን።

## 2. በሥነ ጽሑፍ አማካይነት መመስከር

ሀ. ሥነ ጽሑፍ በወንጌል ሥራ ውስጥ ጠቃሚ ነው። ለሰዎች መናገር እንድትችሉ መንገድ ያዘጋጅላችኋል።

ለ. ሥነ ጽሑፍ ስትመሰክሩ የተናገራችሁትን ያጠናክረዋል።

ሐ. ስትመሰክሩና ስታስተምሩ ያላብራራችኋቸውን ነጥቦች ሥነ ጽሑፍ ግልጽ በማድረግ ይደግፋችኋል።

በሥነ ጽሑፍ ለመመስከር ምቹ ጊዜ እንድታገኙ ጸልዩ። እግዚአብሔር አጋጣሚ ጊዜ ቢሰጣችሁ የአዲስ ኪዳንን ምርጥ ጥቅሶች በማውጣት ላልዳኑት ሰዎች መስጠት ትችላላችሁ።

## 3. ምክር በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ያለው ድርሻ

<u>ዓላማ</u>፦ መምከር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ለመግለጽና በዚህም አማካይነት አገልግሎታችሁን ለማስፋፋት ወደ እግዚአብሔር እንድትመለከቱ ለማስተማር ነው።

ክርስቲያናዊ ምክር ሰዎች ላለባቸው መንፈሳዊ ችግር ትክክለኛውን መፍትሔ እንዲያገኙ ይረዳል።

ሀ. ስለ ምክር የተሰጡ መሠረታዊ ደንቦች

1. ተመካሪው ሰው እንዲናገር ጊዜ ስጡት።

አንድ ሰው መልካም አማካሪ ለመሆን መልካም አድማጭ መሆን ይኖርበታል። አማካሪው መፍትሔውን ከማግኘቱ በፊት የሰውዬውን ችግር መረዳት ይኖርበታል። ተሰምቶት እንዲጸልይ ችግሩን መረዳት አለበት።

በትዕግሥት ማድመጥ ወዳጅነትን ከማጠናከሩም በላይ ፍቅርን ያሳያል። ችግሩን በቃላት ገልጾ ማቅረብ ሰውዬው ያለበትን ችግር እንዲረዳ ያደርገዋል።

2. የራሳችሁን ሁኔታዎችና ስሜቶች ጠብቁ

በችግሩ የተረበሻችሁና ያዘናችሁ መሆናችሁ በፊታችሁ ላይ እንዳይነበብ ተጠንቀቁ።

ልባዊና ትዕግሥተኛ ሁኑ፤ ፍቅርም ይኑራችሁ። መላቅጥ ካጣ ስሜት ተጠበቁ። ወንዶች ወንዶችን፥ ሴቶች ሴቶችን ቢመክሩ መልካም ነው።

3. ምሥጢር አባካኝ አትሁኑ

ምክር የምትሰጧቸው ሰዎች በእናንተ ላይ የጣሉትን እምነት አታጥፉ። በጸሎትም እንድትረዷቸው በእምነት ያካፈሏችሁን ጉዳይ ለሌላ ሰው አትናገሩ።

4. ለምክር ሰጪዎች በተዘጋጀው መመሪያ ላይ ዘወትር አትደገፉ

ሰዎች በአስተሳሰባቸው የተለያዩ ናቸው። ችግሮቻቸው ተመሳሳይ ቢሆንም እንኳ አንዳንዶቹ ከሌሎች የበለጠ ግልጽ ስለሚሆኑ ምክር ለመስጠት ያመቻሉ። መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳችሁ በጸሎት ጠይቁ። ጥቅሶቹን አስቀድማችሁ ካጠናችኋቸው መንፈስ ቅዱስ ተፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሊያስታውሳችሁ ይችላል።

5. በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ ምክር አቅርቡ

መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን ለማሳየት በእግዚአብሔር ቃል ይጠቀማል። እንዲሁም እናንተ ስትመክሩ መንፈስ ቅዱስ በቃሉ ይጠቀማል። ምክር የሚሰጠው ሰውዬ ቢቻል ከቃሉ ማንበብ ይገባዋል። ካልተቻለ ግን እናንተ አንብቡለት።

6. ለአማካሪነት የሚያስፈልጓችሁን ነገሮች አዋቂዎችን ጠይቁ

ማንም አማካሪ ቢሆን ለችግሮች ሁሉ መልስ ሊያገኝ አይችልም። ስለማናውቃቸው ነገሮች ምክር ብንሰጥ ጉዳት እናደርሳለን። ምክር ጠያቂ የሆነውን ሰው ወደ አንድ የቤተ ክርስቲያን እረኛ ወይም ወደ በሰለ ክርስቲያን ሄዶ እርዳታ እንዲያገኝ ገፋፉት።

ለ. ለመምከር ምቹ የሆኑ ጊዜያት

መመስከርና መምከር ብዙ ጊዜ አብረው የሚሄዱ ናቸው።

1. በቤታችሁና በአካባቢያችሁ

2. በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ

3. በመሥሪያ ቤታችሁ

4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ።

ሰዎች ምክርን ይጠይቋችኋል? አንዳንድ ሰዎች በጋዜጣዎች አማካይነት ምክር ያገኛሉ፤ እንዲሁም ብዙዎችም ምክር ለማግኘት በጽሑፍ ይጠይቃሉ። ምክር መስጫ የሬድዮ ፕሮግራም አለ። ለችግሮቻቸውም መልስ ለማግኘት የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ፤ ስለዚህ እነርሱን ለመርዳት የተዘጋጀን እንሁን።

## ጥያቄዎች

1. ክርስቲያን መመስከር ያለበት ለምንድን ነው?

2. ለመመስከር የሚረዱ የተፈጥሮ ምቹ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

3. ሌላውን ሰው ስንመክር ማድመጥ እጅግ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

4. በመመስከር ሥራ ላይ ሥነ ጽሑፍ ምን ያህል ሊረዳ ይችላል?

5. ለምስክርነት የተዘጋጀ አንድ የተወሰነ ደንብ በማጥናት መመስከር የማይቻለው ለምንድን ነው?

# ትምህርት 9

# የቤተ ክርስቲያን እድገት

የወንጌል መስፋፋትና የቤተ ክርስቲያን እድገት

- ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ እግዚአብሔር ያለው ዕቅድ
- ስለ ቤተ ክርስቲያን እድገት ያለው ግዴታ

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት

- በአካባቢው ስትደርሱበት

## 1. የወንጌል መስፋፋትና የቤተ ክርስቲያን ዕድገት

በማቴ. 28፡19–20 «ሂዱ!» የሚለው ትእዛዝ የክርስቶስ ትእዛዝ ነው። መልእክቱን ልናውቀው እንችል ይሆናል፤ ለመስጠትም ችሎታ

ይኖረናል። ስለዚህ መልእክቱን ለሕዝብ ለማድረስ ጥረት ማድረግ አለብን።

ሀ. ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ እግዚአብሔር ያለው ዕቅድ

የእግዚአብሔር ዕቅድ ቤተ ክርስቲያንን መመሥረትና ማሳደግ ነው (ማቴ. 16፥18 አንብቡ)። ኢየሱስ «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ» ብሏል።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ይፈልጋል፤ ይህም እድገት ሦስት ገጽታዎች አሉት። እነርሱም፤

1. ወንጌል ባልደረሰባቸው ስፍራዎች ቤተ ክርስቲያን ማቋቋም
2. የምእመናን ቁጥር እንዲጨምር መጣር
3. አማኞች በእምነት እንዲያድጉና እግዚአብሔርን በማወቅ ለቃሉ እንዲታዘዙ ማስተማር ናቸው።

ኢየሱስ «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ» አለ።

ለ. ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ የግድ መሟላት ያለባቸው ነገሮች

1. መልካም ዘር

እነዚህ ዘሮች የእግዚአብሔር ቃልና ሕዝብ ናቸው። እግዚአብሔር ሕዝቡን በዓለም ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተክሎ ቃሉን እንዲዘሩ ያደርጋል። (ሉቃስ 8፥5–15 እንዲሁም ማቴ. 13፥37–40 አንብቡ።)

2. መልካም መሬት

አንዳንድ ሠራተኞች ቃሉን በየገጠሩ ሲዘሩ ሌሎቹ ደግሞ በከተማ ውስጥ ይዘራሉ። በገጠር ውስጥ ያለው የኑሮ ሁኔታ በከተማ ውስጥ ካለው የተለየ ነው። እያንዳንዱ ሠራተኛ ክርስቶስ ወደ መልካሙ መሬት ሲልከው ፈቃደኛ መሆን አለበት። ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ምቹ የሆነውን መልካም መሬት የሚያውቀው የመከሩ ባለቤት ነው።

እያንዳንዱ ሠራተኛ ወደ ሥራው ሊሄድ የሚነሣበትን ትክክለኛውን ጊዜ የሚያውቀው እርሱ ነው። የአገሩ የጊዜ ሁኔታ ሕዝቡ ስለ ወንጌል ላላቸው ዝንባሌ ወሳኝ ነው። አብያተ ክርስቲያናት በአንዳንድ አካባቢዎች ከሌሎቹ በበለጠ ያድጋሉ። በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚሰጠው የወንጌል ማስፋፋት ዘዴ በሰዎች ላይ ሁልጊዜ የተሻለ ውጤት ላያሳይ ይችላል። ለምሳሌ በአንድ አካባቢ የሚገኙት ሰዎች ማንበብ ሲችሉ በሌላ አካባቢ ያሉት ደግሞ ማንበብ አይችሉም።

## 2. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት

እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በአጥቢያዋ ለሚገኘው ሕዝብ ኃላፊነት አለባት። በአጥቢያ ክልል ውስጥ አዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ለማቋቋም መሞከር አለባት።

እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ሴቶችና ልጆችም ጭምር ክርስቶስን የሚያውቁ ሁሉ ወንጌልን ለማስፋፋት በጣም መትጋት አለባቸው። አንዳንዶች ሰባኪዎች፥ ሌሎች መምህራን፥ የተቀሩት ደግሞ መዘምራን በመሆን ማገልገል ይኖርባቸዋል። ልጆች ደግሞ በእድሜያቸው ክልል ለሚገኙት ወንጌልን መመስከርና ከእነርሱም ጋር በአንድነት መጸለይ ይኖርባቸዋል።

## 3. ወንጌልን በአካባቢ የማስፋፋት ዘዴ

እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ምቹ ጊዜ ባገኘች ቁጥር መሥራት ይኖርባታል።

ሀ. በወንጌላውያን ወንድሞች ወይም ወንጌልን ለማስፋፋት ከአንዱ ወደ ሌላው ስፍራ በሚዘዋወሩ ሰዎች መጠቀም፥

ለ. በግለሰቦች ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወይም ጸሎት ማድረግ፥

ሐ. በአንዳንድ አካባቢዎች ከቤት ውጪ ማለት በሜዳ ላይ ስብሰባዎች ማድረግ ስለሚቻል ይህንን ሁኔታ በመጠቀም ስብሰባዎችን ማዘጋጀት፥

መ. የእሑድ (የሰንበት) ትምህርት ቤቶችን ማቋቋም፥

ሠ. አንዳንድ ጊዜ ሁለት ወይም ሦስት ሆኖ መሰብሰብ ስለሚቻል ይህንንም ዘዴ መጠቀም፥

ረ. ወደ ወኅኒ ቤቶች ሄዶ መመስከር።

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ሕዝቦች የእርሱ ዘር ሊሆኑ የሚችሉት እንዴት ነው?
2. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ላይ ያላት ኃላፊነት ምንድን ነው?
3. በአንዳንድ ሁኔታ ወንጌልን ማስፋፋት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ክርስቲያኖች በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ ያላቸው ኃላፊነት ቀረ ማለት ነው? ምስክር መሆን የሚችሉት እንዴት ነው? ተወያዩበት።
4. የተለያዩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ ላይ ተሳትፎ ሊያደርጉ የሚችሉት እንዴት ነው?

5. እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በሦስቱ አቅጣጫ እንድታድግ የሚፈልገው እንዴት ነው?

## የጥያቄዎች መልስ

### ትምህርት 1

1. ወንጌልን ማስፋፋት ማለት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ኢየሱስ ክርስቶስን ማቅረብ ማለት ሲሆን፥ ሕዝቡም እርሱን አምነውበት እንደ አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉትና በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ውስጥ ገብተው እንደ ጌታቸው እንዲያገለግሉት ነው።

2. እኛ ያገኘነው ሥልጣን በማቴ. 28፡18-20 ላይ ተገልጾአል።

3. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሦስት መሠረታዊ የወንጌል ማስፋፊያ ዘዴዎች ናቸው።

    ሀ. መስበክ ለ. ማስተማር ሐ. መመስከር

4. የወንጌል ማስፋፋትን ሥራ ያቀደው እግዚአብሔር ነው፤ ይኸውም የጠፉትን ሰዎች በመቤዠት ወደ ራሱ ለመመለስ ካለው ዕቅድ ጋር አንድ ነው።

5. ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው።

6. በገጽ 10 ላይ ያለውን ንድፍ ተመልከቱ።

7. ለ፥ ቁ. 1ን ተመልከቱ።

8. ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ።

9. ከዚህ በታች በተጠቀሱት መንገዶች አማካይነት ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ እንችላለን።

    ሀ. ጊዜያችንን በመስጠት፥

    ለ. ገንዘባችንን በመስጠት፥

    ሐ. እንግዶችን በመቀበል፥

    መ. በማስተማር፥ በመስበክ ወይም በሚያጋጥመን ምቹ ጊዜ ሁሉ በመመስከር።

10. አይደለም፤ ሁሉም አንድ ዓይነት ስጦታ የላቸውም።

11. እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ተሳትፎ ማድረግ አለበት፤ ይኸውም እያንዳንዱ አባል እንደተሰጠው ስጦታና ምቹ ጊዜ ነው።

12. እያንዳንዱን የኑሮአችንን ክፍል እግዚአብሔር እንዲቆጣጠር መፍቀድ አለብን።

13. ሰይጣን በጥርጥር፥ በማሳደድ፥ በመረበሽ፥ አለመግባባትን በመፍጠር፥ ተስፋ በማስቆረጥና በሌሎችም ሁሉ ይጠቀማል።

14. ሀ. እኛ መረዳት ያለብን ጦርነቱ ከሰዎች ጋር ሳይሆን ከሰይጣን ጋር መሆኑን ነው።

ለ. የሰይጣንን ዘዴዎች ሁሉ መረዳት አለብን፤ እነዚህንም ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ ይገልጽልናል።

## ትምህርት 2

1. በጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ከሌሎች ሰዎች ጋር በመግባባት እንዲሁም ራሳችንን በማወቅና በመቀበል።

2. ራሳችንን በምንቀበልበት ጊዜ፥

ሀ. የተወሰንን መሆናችንን እንድናውቅ ነገር ግን ይህንኑ የማመኻኛ ምክንያት አድርገን ሳንጠቀምበት፥

ለ. እኛ ራሳችንን ሌላ ሰው ለማስመሰል እንዳንሞክር ስለሚረዳን፤

ሐ. እግዚአብሔር እንደሚወደንና የተፈጠርነውም ለአንድ ዓላማ እንደሆነ እንድናውቅ ስለሚጠቅመን

3. ትችት፥ የበላይነትና ትዕቢት።

4. ስለ ወንጌል መስፋፋት ያሉት መልካም ምክንያቶች፥

ሀ. ሰዎችን ለመርዳት መፈለግ፥

ለ. እግዚአብሔርን ለማስደሰት መፈለግ፥

ሐ. ሰዎችን ለመመለስና ዘላለማዊ ዋጋ ለማግኘት መፈለግ፥

መ. የእግዚአብሔርን ዕቅድና ዓላማ ለመፈጸም መፈለግ።

5. የተሳሳቱ ሁኔታዎችን ወይም ነገሮችን ላለማድረግ አንድ ክርስቲያን ሊጠነቀቅ የሚገባቸው ነገሮች በ«ለ» ቁ. 1፡ ሀ፥ ለ፥ ሐ እና ወዘተ... ዝርዝር ተመልከቱ።

6. ፍቅር፥ ትሕትና በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ውስጥ ሁሉ።

7. በእያንዳንዱ የሕይወታችን ዘመን ሁሉ በሚያጋጥሙን ነገሮች በታማኝነት ለማገልገልና እግዚአብሔር በእኛ አማካይነት እንዲሠራ

መፍቀድ። የእግዚአብሔር ዕቅድ የጠፋትን በፍቅሩና በመንፈስ ቅዱስ አሳምኖ ወደ ራሱ መመለስ ነው።

## ትምህርት 3

1. በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው።
2. ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገው ነገር የተለያየ ነው።
3. መንፈስ ቅዱስ።
4. የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና እርሱንም ማሰላሰል እምነትን ይሰጣል።
5. መንፈስ ቅዱስ ኃይል፥ መንፈሳዊ ፍሬና መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል።
6. ቤተ ክርስቲያንን ማገልገልና ለጠፉት ወንጌልን መስበክ።
7. እያንዳንዱን የኑሮአችንን ክፍል ለእርሱ ብናስረክብ።

## ትምህርት 4

1. በማሰብ ከሚሠራ ሥራ ወይም አገልግሎት ነጻ በሆነ በማንኛውም ጊዜ ልባችንን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ማንሣት ይገባናል፤ እንዲሁም በመንገድ ስንጓዝ ወይም የጉልበት ሥራ ስንሠራ ልንጸልይ እንችላለን።
2. ምስጋና እግዚአብሔርን ያስደስተዋል፤ ተስፋ መቁረጥንም ያስወግዳል።
3. ስንጸልይ እግዚአብሔር በእኛና በሌሎች ውስጥ እንዲሁም በምቹ ጊዜያትም ውስጥ ይሠራል።
4. ጳውሎስ ለግለሰቦች ጸልዮአል፤ እኛም ልንጸልይ ይገባናል።
5. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ የጸሎት ሥርዓቶች ናቸው።

    ሀ. ስለ ማንኛውም ነገር ለእግዚአብሔር መናገር፥

    ለ. በኢየሱስ ስም መለመን፥

    ሐ. ማመንና እግዚአብሔርን ማመስገን፥

    መ. መትጋት፥

    ሠ. በግልና ከሌሎች ጋር መጸለይ፥

ረ. መንፈስ ቅዱስ በጸሎት እንዲረዳን መፍቀድ።

## ትምህርት 5

1. በተሳሳቱ አስተሳሰቦች፥ ስሜቶችና ሥራዎች።
2. ለእግዚአብሔር የመጀመሪያውን ስፍራ አይሰጡትም፤ እንዲሁም ምስጋና አያቀርቡለትም።
3. ሞት።
4. ሀ. እውነትን አለመቀበል፤

   ለ. ለፍቅር ደንታ ያለመስጠት፤

   ሐ. በባለ ሥልጣኖች ላይ ተቃውሞ ማስነሣት።
5. እርሱን እንድናከብርና እንድንወድ ከዚያም በኋላ ዘላለማዊ ክብሩን እንድንካፈል።
6. እግዚአብሔርን በልባችንና በነፍሳችን እንዲሁም በአእምሮአችን ሁሉ መውደድ ነው። ይህንን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተለይቶ ማንም ሊፈጽመው አይችልም።
7. በፍቅር፥ በትሕትና ለሌሎች በማዘን የተሞላ ሊሆን ይገባል።
8. ሀ. መለያየት፥

   ለ. ስሕተት፥

   ሐ. ያለመደሰት፥

   መ. ባርነት፥

   ሠ. ሞት።

## ትምህርት 6

1. ሀ. የደኅንነት መልእክት ስናስተላልፍ እግዚአብሔር ሰዎችን እንደሚወድና ሊያድናቸው እንደሚፈልግ ልናስረዳቸው ይገባናል። እግዚአብሔር ማንንም ሰው ቢሆን አያስገድድም፤ ነገር ግን እርሱን ለሚቀበሉት ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ነው።

   ለ. በማዳን ሥራው ውስጥ ኢየሱስ አራት መንገዶችን አዘጋጅቷል።

1. ኢየሱስ የእኛ አማላጅ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቀናል።
2. እርሱ የእኛ ምትክ በመሆን የኃጢአት ዋጋ የሆነውን ሞት ክርስቶስ በእኛ ፋንታ ተቀበለ።

3. ክርስቶስ የእኛ ነጻ አውጪ ሆኖ የኃጢአትን ኃይል ሰብሮ ነጻነት ሰጠን።

4. ክርስቶስ የእኛ ጌታ ሊሆን ሕይወታችን ዕቅድ እንዲኖረው ያደርጋል። ሕይወታችንንም ይመራዋል።

2. ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት በወንጌል ማስፋፋት ሥራ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻዎች ናቸው።

   ሀ. ኃጢአትን ይገልጻል፤

   ለ. በኃጢአታችን እንድንጸጸት ይረዳናል፤

   ሐ. በልባችን ውስጥ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ተቃውሞ ያስወግደዋል፤

   መ. ከክርስቶስ ጋር አገናኝቶን ብልቶቹ እንድንሆን ያደርገናል፤

   ሠ. ትክክለኛ አስተሳሰብ እንዲኖረንና እንዲሁም ትክክለኛ ስሜቶች በውስጣችን እንዲፈጠሩ ይረዳናል፤

   ረ. ክርስቶስ ከዚህ ከሥጋዊ አካላችን ሊያድነን እስኪመጣ ድረስ ያትመናል፥ (ኤፌ. 1፡13–14)።

3. ስለ ደኅንነታችን ያለብን ኃላፊነት

ሀ. ምንጊዜም እግዚአብሔር ሰው እንዲያምን ስለማያስገድድ እኛ ፈቃደኞች ሆነን መገኘት ያስፈልገናል።

ለ. በኃጢአታችን መጸጸት ይገባናል። የክርስቶስን አዲስ ሕይወት ከማግኘታችን በፊት ከልባችን ልንጸጸት ያስፈልጋል። እኛ ፈቃደኞች ሆነን ከተገኘን መንፈስ ቅዱስ ይህን ያደርግልናል።

## ትምህርት 7

1. ዮሐ. 14፡6፤ የሐዋ. ሥራ 4፡12፤ 1ኛ ጢሞ. 2፡5።

2. ዮሐ. 3፡3–7፤ ኤፌ. 2፡8–9፤ ቲቶ 3፡5።

3. ማቴ. 7፡1–3፤ ሮሜ 2፡1–3።

4. ሀ. ከሰው ምስጋና ለመቀበል መሻት፤

   ለ. የዚህ ዓለም ምቾት፤

   ሐ. ሀብት፤

   መ. የዚህ ዓለም ክብር።

5. ያዕ. 4፡13-14፤ ኢሳ. 55፡5፤ ምሳሌ 27፡1፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡2 አንብባችሁ ተረዱ።

6. ማር. 8፡34-38፤ ሉቃ. 6፡22-23።

7. 2ኛ ቆሮ. 12፡9፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡13፤ ሮሜ 8፡31-39 አንብባችሁ ተረዱ።

8. ጥቅሶች

ሀ. ማመን፡- ዮሐ. 3፡16፤ የሐዋ. ሥራ 16፡31።

ለ. ኃጢአትን መናዘዝ፡- 1ኛ ዮሐ. 1፡9።

ሐ. ይቅርታ ማድረግ፡- ሉቃስ 18፡13።

መ. ክርስቶስን መቀበልና መመስከር፡- ሮሜ 10፡9-10።

ሠ. መከተል፡- ሉቃስ 9፡23።

## ትምህርት 8

1. ሌሎችም ስለ ክርስቶስ እንዲሰሙ የእግዚአብሔር ዕቅድና የክርስቶስ ትእዛዝ ነው።

2. ከብዙዎቹ መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፥

- በቡና ሰዓት የሚደረግ ጭውውት፥
- ቤት ለሚመጡ እንግዶች፥
- በቤት ውስጥ የሚደረግ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወይም የጸሎት ጊዜያት።

3. አንድ ሰው ያለበትን ችግር ከመስማታችን በፊት ምክር ልንሰጠው ስለማንችል ነው።

4. ሥነ ጽሑፍ

- ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል ጥማት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
- ከዚህ በፊትም የሰጠነውን ምስክርነት ሊያጠናክርና ሊደግፍ ይችላል፤
- ግልጽ ያላደረግናቸውን ነገሮች ሁሉ ሊያብራሩ ይችላሉ።

5. እያንዳንዱ ሰው የተለያየ ስለሆነ ስለ መመስከር ወይም ወንጌልን ስለ ማስፋፋት የተሰጠ የማስተማር ደንብ የለም።

## ትምህርት 9

1. እነርሱንም እግዚአብሔር በተለያየ ስፍራ ስለተከላቸውና በዓለምም ውስጥ ለመመስከርና ቃሉን ለመዝራት ስለመደባቸው ነው።

2. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባሎችዋ ሁሉ በራሳቸው ቤት ብቻ ሳይሆን በሌሎች ስፍራዎችም ውስጥ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል በመመስከር ሥራ ላይ ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ ይኖርባታል። አንዳንዶች በጽሑፍ፥ ሌሎች በመስበክ፥ የተቀሩት በማስተማር፥ ጥቂቶቹ በቤታቸው ውስጥ በመመስከር፥ ብዙዎቹ በመዘምራን ቡድን ውስጥ በመሳተፍ፥ ሁሉም በዕድሜና በዖታ ክልላቸው ውስጥ ስለ ክርስቶስ እንዲናገሩ ማድረግ አለባት። ሁሉም ተሰጥተው ሊያገለግሉና ሊጸልዩ ይችላሉ።

3. አይቀርም።

4. የ 2ኛውን ጥያቄ መልስ ተመልከቱ።

5. – ወንጌል ባልተዳረሰባቸው ስፍራዎች ቤተ ክርስቲያንን በማቋቋም፥
   - የምእመናን ቁጥር በመጨመርና
   - መንፈሳዊ ብስለት እንዲኖራቸው በማድረግ።